


[illegible] ቅ.ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን



ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ታተመ

# ትንሣኤ



የብርሃናተ ዓለም ጴጥሮስ ወጳውሎስ ቤተ ክርስቲያን

፻፲፱ ቁጥር

ግንቦት ፲፱፻፸፱ ዓ.ም

www.ethiopianorthodox.org

«ይህ መጽሔት የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፤ ሥርዓትና ዜና ፤ ልማትና የግብረ ገብነት ትምህርት በተግባር ጥምር እንዲተረጐሙ ለሥራ እንነሣ የሚል ስለሆነ "ትንሣኤ" ተብሎ ተሰይሟል ። »

ዋና አዘጋጅ ቀ. ልሣነ ወርቅ በዛብህ
ም/ አዘጋጅ መ/ ክኅረ. ርግብ ማርቆስ


በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ የሥነ ጽሑፍ ክፍል ተዘጋጅቶ በወር አንድ ጊዜ እየታተመ የሚወጣ ።

የስልክ ቁጥር 110754
የመልእክት ሣ. ቁ. 3137
አዲስ አበባ ፤

# ማውጫ

**አርእስት** **ገጽ**

ደብዳቤዎች ........ ፩
ርእሰ አንቀጽ ቅዱስ ያሬድና
ዘመነ ፋሲካ ........ ፪
ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት
ያስተላለፉት ቃለ ምዕዳን ........ ፬
እመ ብርሃን ተወለደች ........ ፮
ዜና ሊቃውንት ........ ፯
የዓለም አብያተ ክርስቲያናት
ኮሚቴ ያስተላለፉቸው ውሣኔዎች ........ ፱
ልማት በቤተ ክርስቲያን ........ ፲፩
ግበሩ በዓለ በትፍሥሕት ........ ፲፫
የእግዚአብሔርን ቸርነት ተናገሩ ........ ፲፭
የእየሳ ቅዱስ ሚካኤል
ቤተ ክርስቲያን ታሪክ ........ ፲፮
ዕለተ ምሳሌ ........ ፲፯
የአብርሃ ወአጽብሐ ታሪክ በአጭሩ ........ ፲፱
አባ ቁራይ ........ ፳፪
የ7ኛው ሰበካ ጉባኤ ሥምረት
በባሌ ሀ ስብከት ........ ፳፫




የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ጠቅላይ ቤተ ክህነት ለስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ አዲስ አበባ ፡

በሀገራችን በከተማም ሆነ በገጠር ቀደም ብለው የተሣሉትም ሆኑ አሁን የሚሣሉት አንዳንድ ሥዕሎች የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነትን የሚያንፀባርቁ ናቸው ፡ በተለይም የሥላሴ ሥዕል ሦስቱ አካላት ተጠጋግተው የእጅቻውና የእግራቸው አቀማመጥ አንድ ዓይነት ሆኖ ዓለምን በመካከለኛው እጅ አስቀምጠው በግራና በቀኝ ያሉትን ደግፈው ነበር የሚሣሉት አሁን ግን የሚሣለው የሥላሴ ሥዕል ለአንዱ አካል አንድ ዓይነት ልብስ ለሁለተኛው ሌላ ለሦስተኛው እንዲሁ ሌላ ዓይነት ልብስ ለብሰው ሲሣሉ የእጅና የእግር አቀማመጣቸው የተለያየ ነው ።

ለዚህም የሥዕል ስሕተት የመጀመሪያውን ደረጃ ይዞ የሚገኘው በመንበረ ፀባዖት ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል ጣራ ላይ የተሣለው ነው ብንል ድፍረት አይሆንም በዚህ ካቴድራል የተሣሉት አንደኛው ሥዕል ቀኝ እጁን አውጥቶ ግራ እግሩን አስቀድሟል ሁለቱ አካላት ሥዕሎች ደግሞ ግራ ግራ እጃቸውን አውጥተዋል የመካከለኛው አካል ቀኝ እግሩን አስቀደሟል በጠቅላላው በቅድስት ተዋህዶ እምነታችን መሠረት አንድ ፈቃድ አንድ ሥልጣን አንድ መንግሥት አንድ ባሕርይ ብላ የምታምን ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴ የተሣለውን ሥዕልና የመሳሰሉትን ዘመን አመጣሽ ሥዕሎች ትቀበላቸዋለችን?

ስለዚህ ከዚህ በላይ እንደገለጽኩት ትክክለኛ ነው ተብሎ ይታመን በት እንደሆነ ትክክለኛነቱን የሚያረጋግጥ ማስረጃ እንዲጻፍልኝ ፡ ትክክለኛ አይደለም ከተባለ ደግሞ ስሕተቱ በትንሣኤ መጽሔት ተብራርቶ እንዲገለጽ አሳስባለሁ ፡

ከምእመናን አንዱ
አክሊሉ ቢረሳው

መልስ

አቶ አክሊሉ ቢረሳው ስላቀረቡልን ጥያቄ በጣም እናመሰግናለን የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን አባል የሆኑ ሁሉ በቤተ ክርስቲያናችን የሚደረገውን አንዳንድ ጉድለት በገለልተኛነት ተመልክቶ ማለፍ አይገባውም ከሚመለከተው ክፍል ጠይቆ ጉዳዩን መረዳት አለበት ።

ወደ ጥያቄው መለስ እንበልና ጥያቄው ተገቢ ስለሆነ እኛም ተገቢውን መልስ እንስጣለን ሥላሴ በስም በግብር በአካል ሦስት ሲሆኑ በባሕርይ፡ – በህልውና በፈቃድ በመለኮት በመሳሰሉት አይለያዩም አንድ ናቸው ፤ ሥላሴ በመጀመሪያ ጊዜ ተገልጸው የታዩት በአብርሃም ቤት ነው በዚያ የተገለጹትም በሦስት ሰዎች አምሳል መሆኑን ቅዱስ መጽሐፍ ያስረዳናል ፤

ቢሆንም ይህንን ይመስላሉ ይህንን ያህላሉ ብሎ ለሥላሴ ምሳሌ ለመስጠት አይቻልም፡– ቢሆንም ሰው በጆሮ ከሚሰማው ቃል ጋር በዓይኑ ዓይቶ ለመረዳት እንዲችል ሲሉ ሊቃውንት የሚያስተምሩትን ትምህርት በሥዕል መልክ እየነደፉና እየሳሉ በማቅረብ ምእመናን እንዲያምኑት እንዲረዱ ፡ ማድረጋቸው የተረጋገጠ ነው ።

በዚህም መሠረት የሥላሴን ሥዕል ሲሥሉ በማንኛውም ነገር ሳያበላለጡ ፡ በሽማግሌዎች አምሳል ይሥሏቸዋል ፤ በአንዳንድ ቦታ ዓለምን ለሦስት ይዘው ተሥለው ይገኛሉ ፡ ከዚህ በስተቀር በመልክም በቁመትም የተለያየ ሁኔታ አይታይባቸውም ፡ ሊታይባቸውም አይገባም፡

ጠያቂው ለስሕተቱ መነሻ አድርገው የጠቀሱት የመንበረ ፀባኦት ቅድስት ሥላሴን የጠፈር ግርጌ ሥዕል ስለሆነ በጥያቄውም መሠረት እኛም ሁኔታውን ለማረጋገጥ ሄደን ተመልክተነዋል አቀማመጣቸውም ሆነ ዓለምን አያያዛቸው ከቤተ ክርስቲያናችን እምነትና ባህል ጋር የተያያዘ መስሎ አይታይም ሠዓሊውን አግኝተን ባንጠይቃቸውም በዚህ ሞያ ተሠልፈው የሚሠሩትም ሆኑ የቤተ ክርስቲያናችን ሊቃውንት እንደዚሁ ያለውን የሥዕል አቀማመጥ የማይደገፉት መሆናቸውን ገልጸውልናል ለእኛም ቢሆን የሥዕሉ አቀማመጥ ትክክል መስሎ አልታየንም ።

ስለዚህ ጠያቂው አቶ አክሊሉ ቢረሳው እንዳሳሰቡት ሥዕሉ እርማት ቢደረግለት መልካም ነው በማለት መልሳችንን እናጠቃልላለን ።



www.ethiopianorthodox.org

# ቅዱስ ያሬድና ዘመነ ፋሲካ

ፋሲካ ማለት ማዕዶት ማለት ነው ማዕዶት ማለት ደግሞ መሸጋገሪያ ድልድይ ማለት ነው ። ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሰማየ ሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ተወልዶ ተሰቅዬ ሙቼ ተነሥቼ አድንኃለሁ ሲል በሰጠው ተስፋ መሠረት ያደረገልንን ቸርነት የዋለልንን ውለታ እያስታወስን መዋዕለ ትንሣኤውን ወይም የፋሲካን ሰሞን እናከብረዋለን ።

በስድስተኛው መቶ ክፈለ ዘመን በዓፄ ገብረ መስቀል ዘመነ መንግሥት ተንሥቶ የነበረው የሀገራችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድ በገብረ መንፈስ ቅዱስ እየተቃኘ ለቤተ ክርስቲያናችን መገልገያ የሆኑትን ፀዋትወ ዜማ ደርሷል ፀዋትወ ዜማዎችንም የደረሰው በሦስት ክፍሎች ሲሆን እነርሱም ግዕዝ ዕዝል ዓራራይ ናቸው ደመ

ቅዱስ ያሬድ የፀዋትወ ዜማዎችን ጣዕመ ለዛ የነሣው በተመስጦ ወደ ላይ በማረግ ከ፳፬ ካህናተ ሰማይ መሆኑ ቢታመንም ከተጠቀሱት የዜማ ዓይነቶች የተለየ ሌላ ዜማ አለመኖሩ የተረጋገጠ ነው ፡ አንዳንድ ሊቃውንት ግን "ዋይ ዜማ ዘሰማዕኩ በሰማይ እንዘ ይዜምሩ መላእክት መላእክት በሰማይ ሲዘምሩ የሰማሁት አየ ዜማ" የሚለውን ቃል መሠረት በማድረግ ቅዱስ ያሬድ መላእክት ሲዘምሩ የሰማውን ዜማ ሁሉ በጠቅላላ ለመዘመር እንዳልቻለ ይናገራሉ ።

ይሁን እንጂ እግዚአብሔር የፈቀደለትን ያህል የዜማ ዓይነት ለቤተ ክርስቲያናችን መገልገያ እንዲሆን አጣፍጦና ቀምሮ አዘጋጅቶ ስለተወልን ልናመሰግነውና መታሰቢያም ልናደርግለት ይገባናል ይህ ሊቅ ወለመንፈስ ቅዱስ ቀዳሚሃ ለጽዮን ሰማየ ሣረረ ወበ ዳግም አርአያ ለሙሴ ዘክመ ይገብር ገብረ ለደብተራ" ወደ አማርኛ ሲተረጎም ለአብ ለወልድ ለመንፈስ ቅዱስ ምስጋና ይገባል የጽዮን አምሳያ በመጀመሪያ ሰማይንና ምድርን ፈጠረ ዳግመኛም ለሙሴ ደብተራ ኦሪትን እንደተ አድርጉ መሥራት እንደሚገባው አሳየው ማለት ነው(ዘፀዓ ፳፭.፰)

ይህንንም የመጀመሪያውን የምስጋና ቃል ቅዱስ ያሬድ አርያም ብሎ ሠይሞታል ። ሊቁ ቅዱስ ያሬድ ከዓመት እስከ ዓመት የሚዘመረውን እንዲሁም በበጋ በክረምት በመጸው በፀደይ እየለያየ ለጿማትን በዓላትን ሰንበታትን የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያምን የመላእክትን የጻድቃንን የሰማዕታትን መታሰቢያ በዓላት በመመልከት የደረሰው ፀዋትወ ዜማ እጅግ የሚያስደንቅና የሚያስደስት ነው ።

ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን በአሁኑ ጊዜ የምትገለገለው በቅዱስ ያሬድ ፀዋትወ ዜማ መሆኑ የታወቀ ነው ። የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያናችን ከሚያስመሰግኗት ባሕሎቿም አንዱ የቅዱስ ያሬድ ጣዕመ ዜማ መሆኑ ታውቋል ። የሊቁ ዜማ በቤተ ክርስቲያን ሲዘመር እንኳን ምሥጢሩን ለሚያውቁና ለሚረዱ ለማያውቁትም ቢሆን ልቡናን ይመስጣል ።

ከታሪክ እንብበን እንደተረዳነው ቅዱስ ያሬድ በሚዘመርበት ጊዜ ዓፄ ገብረ መስቀል በጣዕመ ዜማው ልቡናቸው ተመስጦ በትረ መንግሥታቸውን በቅዱስ ያሬድ እግር ላይ ስላሳረፉበት የቅዱስ ያሬድ ሰገር በደም ታልሎ እንደነበር ተጽፎአል በተጨማሪም በጉንደር ከተማ በስተሰሜን በሚገኘው ወገራ በሚባለው ሀገር ቅዱስ ያሬድ አንድ ገበሬ በሚያርስበት አጠገበ ቆሞ ሲዘምር የሚያርሳቸው በሮች ከመዝሙሩ ጣዕም የተነሣ አንታረስም በማለታቸው ገበሬው ተበሳጭቶ ቅዱስ ያሬድን በጅራፍ ገርፎታል ይባላል ።

ይህ ሁሉ የሚያስረዳው የዜማውን ለዛና ጣፋጭነት ነው ።

ጥሬው ዜማ ተቃኝቶ ሲዘመም ሲጸነጸል ሲመረገድና ሲለዘብ ሲዋረብ በመጨረሻም ሲጸፋ ያለው ጣዕምና ለዛ በምድር ዓለም መኖርን አስረስቶ ወደ ሰማያዊ ዓለም ይጋብዛል ።

አባቶቻችን ሊቃውንት በመዋዕለ ፋሲካ ጦም አትዋሉ ዘር ግን አትምተሩ ይላሉ በዕርገጥ የሚያርስ የሚዘራና የሚያመርት ሰው በሰኔና በግንቦት የሚዘራውን ዘር አስቀምጦ ጦሙን እንዳይውል እንዲበላና እንዲጠጣ ተፈቅዷል አምሳ ቀን ጸማቸሁ ዓርብንና ረቡን ሳትለዩ መዳዳሙን ብሎ ይላል ፍ ነ ።

በመዋዕለ ፋሲካ በቤተ ክርስቲያናችን የሚዘመረው መዝሙርም የጌታችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስን አዳኝነት የሰውን ልጅ ነፃነት የሚያበሥር መሆኑ ከላይ ተገልጿል የፋሲካ ሰሞን የሚከበረው በቤተ ክርስቲያን መዝሙር ብቻ አይደለም ዘመድ ከዘመዱ ጉረቤት ከጉረቤቱ የሩቁ ከቅርቡ ጋር የሚገናኘውና አብሮ የሚበላውና የሚጠጣው በፋሲካ ሰሞን ነው ።

እንደተለመደው ባህላችንም ልጆች ለአባቶችና ለእናቶች የአክፋይ ስጦታ የሚሰጡት አባቶችና እናቶችም ስጦታውን ተቀብለው ቡራኬን ለልጆቻቸው የሚያስተላልፉት በዘመነ ፋሲካ ነው ስጦታን ለአባቶች አቀርቦ ቡራኬ መቀበልም ከጥንት ጀምሮ ሲያያዝ የመጣ ነው እንጂ እንደ እንጉዳ ደራሽ እንደ ውሃ ፈሳሽ አይደለም ።

ለማስረጃ ይሆነን ዘንድ ከመጽሐፍ ቅዱስ እንመልከት አብርሃም ነገሥተ ኮሎዶጎምርን ድል አድርጉ ሲመለስ መልከ ጼዴቅ ኅብስተ በረከት ጽዋዓ አኩቴት ይዞ በተቀበለው ጊዜ አብርሃም ከገንዘቡ አሥር አንድ አውጥቶ ሰጥቶታል ዘፍ ፲፬.፳፫

እንዲሁም ዮሴፍ በሰመገለ ጊዜ ያዕቆብ ጠቦቱን አርዶ አወራርዶ ምግቡን በሚገባ አዘጋጅቶ አምጥቶ ለአባቱ ባቀረበ ጊዜ አባቱ ዮሴፍ የልጁን የያዕቆብ ስጦታ ተቀብሎ ቡራኬውን ሰጥቶታል ።

ባህሉንና ወጉን ሥነ ሥርዓቱን ሳይለቁ ለአባቶች የሚቀርበው መንፈሳዊ ስጦታ የሚነቀፍ ሳይሆን የሚመሰገን ነው በመጽሐፍ ቅዱስም የተደገፈ መሆኑን ገልጸናል ።

ግን ዓላማውን መሳት አይኖርበትም በስጦታ አሳቦ የማይገባ ከባድ ስጦታ ማቅረብ ተገቢ ስላልሆነ መጠንቀቅ ያስፈልጋል ። በዚህ ሰሞን በክርስቶስ ሞት እኛ መዳናችን በክርስቶስ መነሣት እኛ ትንሣኤ ሕይወት መነሣታችን እያስታወስን በፍቅርና በትሕትና አብረን በመብላትና በመጠጣት የተራቡትንም በማብላትና በማጠጣት መዋዕለ ፋሲካውን ልናሳልፈው ይገባናል።

የሀገራችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ፋሲካ ማለት መሸጋገሪያ ማለት ነው በእርሱም ከሞት ወደ ሕይወት ተሸጋገርናል ብሎ እንደዘመረው የእኛም መዝሙር በወርኃ ትንሣኤ ይኸው መሆን አለበት ።

www.ethiopianorthodox.org

# ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ የትንሣኤን በዓል ምክንያት ብማድረግ በቴሌቪዥንና በራድዮ ያስተላለፉት ቃለ ምዕዳን

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ።

በገጠርና በከተማ የምትኖሩ የሀገራችን የኢትዮጵያን ዳር ድንበር ለመጠበቅና ለማስከበር በባሕርና በየብስ ያላችሁ በሆስፒታል የምትገኙ ሁሉ ፡ ሁሉን የፈጠረ ለሰው ሁሉ ቤዛ የሆነ በሰማይም በምድርም ያለ ሕያው እግዚአብሔር አምላካችን እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው በሰላም አደረሳችሁ ።

"ይትባረክ እግዚአብሔር አቡሁ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ ዘወኀደነ በብዝኃ ምሕረቱ ለተስፋ እንተ ባቲ ነሐዩ በተንሥኦቱ ለእግዚእነ ኢየሱስ ክርስቶስ እምነ ምውታን"።



ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ቃለ ቡራኬ ሲያስተላልፉ

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ከሙታን ተለይቶ በመነሣቱ የማይጠፋውንና የማይለወጠውን ለሰው ልጆች በሰማይ የተጠ በቀውን የመንግሥተ ሰማያትን ክብር ለመውረስ ሁለተኛ የወለደን እግዚአብሔር አብ ይክበር ይመስገን ፩ኛ ጴጥ.፩.፲ ።

ይህ ዕለት የሰው ልጅ ከኃጢአት ቁራኛነት ተለይቶ በጽድቅ ታድሶ አዲስ ሰውነትን ለብሶ እንዲኖር በሰውና በፍጥረት ላይ የተ ላለፈው መርገመ ሥጋና መርገመ ነፍስ የተሻረበት ዕለት ነው ። አዳም ሲፈጠር የፍጥረታት ሁሉ ገዥ ሆኖ ፈጣሪውን እያመሰገነ ሞት በሌለበት አዲስ ሕይወት እንዲኖር ነበር ። ነገር ግን የተሰጠው ነፃነቱ ወደ ራሱ ፈቃድ ስለመራው የእግዚአብሔርን ትእዛዝ ተላለፈ ፡ በኃጢአት ወደቀ ፡ ከክብር ወደ



ሐሣር ደረሰ ። ኃጢአትና ሞት ስለጠኑበት ኃጢአትም የእግዚ አብሔርን ፈቃድ ባለመፈለግ ከፈጣሪ ተለይቶ በራሱ መንገድ መሄድ በራስ ፈቃድ መመራትና መኖር ነው ይህንንም ነቢዩ ኢሳይያስ እኛ ሁላችን ተቅበዝብዘን ጠፋን ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ ። እግዚአብሔርም የሁላችንን በደል በእርሱ ላይ አኖረ ብሎአል (ኢሳ ፶፫.፮)

ፈጣሪያችን እግዚአብሔር ሰውን ከማፍቀሩ የተነሣ በቸርነቱ ብዛት ለሰው ልጆች ሁሉ ድኅነትን ለመስጠት በሰጠው ተስፋ የባሕርይ ልጁ እግዚአብሔር ወልድ በሰው ባሕርይ ተገለጠ ። እርሱም ድኅነትን ለሚፈልጉ ለኃጢአተኞች ሥርየተ ኃጢአትን ለርኁባነ ሥጋ ምግብን ለርኁባነ ነፍስ ትምህርትን እየመገበ በሰዎች መካከል ተመላለሰ ፡ በደላችንን ተሸከመ ታመመ ተሰቀለ ፡ ሞተ ፡ በሦስተኛውም ቀን ሙስና መቃብርን አጥፍቶ ሞትን ድል ነሥቶ ተነሣ ፡ በትንሣኤውም የዓለምን ድኅነት ፈጸመ ። ስለዚህም ወንጌላዊው ዮሐንስ "እግዚአብሔር አንድ ልጁን እስኪሰጥ ዓለሙን እንዲሁ ወዶታልና ዓለም በልጁ እንዲድን እንጂ በዓለም እንዲፈርድ እግዚአብሔር ልጁን ወደ ዓለም አላከውም" ይላል (ዮሐ ፫፡ ፲ ።)

በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ ከሞት ወደ ሕይወት ከኃጢአት ወደ ጽድቅ ተሸጋገርናል ከኃጢአት ፍርሃት ወጥተን ሰላምን አገኘተናል ከፈጣሪያችን ጋር ታርቀን ወደ እርሱ ቀርበናል ። እናንተ በፊት ርቃችሁ የነበራችሁ በክርስቶስ ደም ቀርባችኋል እርሱ ሰላማችን ነውና" ይላል ቅዱስ ጳውሎስ (ኤፌ ፪.፲ ።)

ስለዚህ በመንፈሳዊ ሕይወት ታድሰን በአዲስ ሕይወት እንመላለስ ። ሐዲስነት በአእምሮ በመንፈስ ሁልጊዜ ያለማቋረጥ በክርስቶስ መታደስ ነው ። ሐዲስ የሚያሰኘውም እግዚአብሔር በእውቀትና በንጽሕና ያደሰውን ሰውነት ገንዘብ አድርጉ መልካም ሥራ መሥራት ነው ። ቅዱስ ጳውሎስ "በአእምሮአችሁ መንፈስ ታደሱ ማንም በክርስቶስ ቢሆን አዲስ ፍጥረት ነው ። አሮጌው ነገር አልፎአል ፡ እነሆ ሁሉም አዲስ ሆኖአል" ይላል ኤፌ ፬.፳፬ ፡ ፪ ቆሮ ፭.፲፯ ።

እንግዲህ በክርስቶስ ሕይወት ታድሰን ሕያዋን ሆነን ለመኖር መልካም ሥራ እንሥራ ። እግዚአብሔር አንድ ልጁን ለሞት አሳልፎ ለሰጠላቸውና በልጁ ሞት ይቅርታ ላደረገላቸው ለሰው ልጆች ሕይወት ማሰብ ይገባናል። አሳዳጊ የሌላቸው ሕፃናት ምግብ ልብስ ትምህርት አግኝተው እንዲያድጉ ፡ ረዳቱ የሌላቸው አረጋውያን እንዲረዱ ማድረግ ክርስቲያናዊ ግዴታ ነው ። እግዚአብሔር ለእኛ መልካሙን እንዳደረገልን ሁሉ ለሌሎች መልካም እንድናደርግ ታዞናል (ማቴ ፯.፲፪ ።)

ስለዚህ ርስ በርሳችን እየተረዳዳን በሃይማኖት በፍቅር ጸንተን አምላካችንን ዘወትር በጸሎት እንለምነው ። ጸሎት ምድራዊ ፍላጎትን የነፍስ ድኅነትን የሚያስገኝ ኃይል ነው ። በፍቅር አንድ ሆነን ስንጸልይ ፈጣሪያችን ጠለምሕረትን ያወርድልናል እክለ በረከትን ይሰጠናል ። በሕይወትም ይጠብቀናል ። ምሕረት የባሕርይ ገንዘቡ የሆነ አምላካችን "ለምኑ ይሰጣችኋል ፈልጉ ታገኟላችሁ" ብሎአልና (ማቴ ፯.፯—፲ ።) የሰላም አምላክ ለዓለም ሁሉ ሰላምን ይስጥልን በዓሉን የደስታ ያድርግልን አገራችንን ኢትዮጵያን ለዘለዓለም ይባርክ

አሜን ።

## እመ ብርሃን ተወለደች

ድንግል ማርያም የድኅነት መሠረት የሕይወት መሰላል የጽድቅ ድል ድይ ወዘተ መሆኗ ከመወለዷ ቀደም ብሎ ተነግሮ ነበር በመቅደመ ተአምሯ ላይ አዳም አባታችን ከሔዋን ከሚስቱ ማኅፀንና ከእርሱም አብራክ ድንግል ማርያም እንደምትወለድ በመንፈስ ቅዱስ አውቆ ሔዋንን ሕይወቱ ይላት እንደነበር ተጽፎ አል።

የድንግል ማርያም አባቷ ኢያቄም እናቷ ሐና ይባላሉ አንድ ወንድ ለአንዲት ሴት አንዲት ሴት ለአንድ ወንድ ትብቃ በተባለው ሕግ ጸን ተው ይኖሩ ነበር ፡ ነገር ግን ልጅ ስላልነበራቸው ለልባቸው ተስፋ ለሚ ያደርጋቸው ማረፊያ የሚሆን ልጅ እንዲ ሰጣቸው ዘወትር ወደ ፈጣሪያቸው ይጸልዩ ነበር ።

ከዕለታት አንድ ቀን ሁለቱም ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሔደው ጸሎት አድርገው ወንድ ልጅ ብትሰጠን ቤተ መቅደስን እያገለገለ ጧትና ማታ እያወደሰ በዚሁ ቤተ መቅደስ ይኖራል እንጂ እኛን ይርዳን ያገልግ ለን አንልም ሴት ልጅም ብንወልድ መሶበ ወርቅ እየሰፋች መጋረጃ እየፈ ተለች በማገልገል ትኖራለች እንጂ ትርዳን ታገልግለን አንልም ብለው ተስለው ወደ ቤታቸው ተመለሱ ።

እግዚአብሔር አምላክም የለመኑ ትን የማይነሣ የነገሩትን የማይረሣ ነውና ስእለታቸውን ሰማቸው ወዲያው ድንግል ማርያም ተፀነሰች ሐና ድንግል ማርያምን እንደፀነሰች የእክ ስቷ ልጅ ሞተ ትወደው ነበርና ከእስ



www.ethiopianorthodox.org

ከሬት አጠገብ ቁማ ስታለቅስ ጥላዋ ቢያርፍበት ተነሥቶ "ሰማይና ምድርን ለፈጠረ አያቴ ሆይ ሰላምታ ይገባሻል" ብሎ ተናግሮ ተመልሶ አርፎአል እንዲሁም ለሐና አንድ ዓይና የሆነች አክስት ነበረቻት ሐና እግዚአብሔር በረድኤት ጐበኘሽ መሰለኝ ብላ ሰውነቷን ዳስሳ ዓይኗን ብትነካው በርቶላታል በቅርብ ሆነው ጉዳዩን ይከታተሉ የነበሩ አይሁድ በሐና ላይ በጠላትነት ስለተነሡባት ወደ አድባረ ሊባኖስ ሸሽታ ሄዳ በዚያ ወልዳታለች በዚህም ጊዜ እምሊባኖስ ትወጽእ መርዓት ከሊባኖስ ሙርዓት ትወጣለች ተብሎ በነቢይ የተነገረው ተፈጽሟል ።

እመቤታችን ድንግል ማርያም በተወለደችበት አካባቢም እስከ ፫ ቀን ብርሃን ሆኖአል የሐናና የኢያቄም ዘመዶችም ሊጠይቋቸው ሲመጡ ዳቦ እየጋገሩ ንፍሮ እያነፈሩ ይዘው መጥተዋል ይህም ልማድ ሳይዘነጋ ስለመጣ አሁንም የግንቦት ወር ሲገባ ሁሉም በየቤቱ ንፍሮ አንፍሮ ዳቦ ጋግሮ በመሰብሰብ ይመገባል ትርጉሙን ያልተረዱ አንዳንድ ሰዎች ግን ወደ ልዩ ልዩ አምልኮት በመለወጥ የማይገባ ሥራ ሲፈጽሙበት ይታያሉ ይህም የማይገባ አስነዋሪ ተግባር ስለሆነ መንፈሳዊውን በዓል ወደ አምልኮ ባዕድ ለውጠው የሚያሚርቱ ሁሉ ከመጥፎ ተግባራቸው እንዲቆጠቡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን መንፈሳዊ ምክሯን ከማስተላለፍ አትቆጠብም ።

ወደ ተነሣንበት ታሪክ እንመለስና ድንግል ማርያም በተወለደች በሦስት ዓመቷ ወላጆቿ ኢያቄምና ሐና ይዘዋት ወደ ቤተ መቅደስ ሄዱ ቤተ መቅደሱን የሚያስተዳድረው ዘካርያስ ይባል ነበር ይህቺን ብላቴና የወለድናት ተሥለን ነውና እንካ ተቀበለን አሉት ዘካርያስም ይህችን ሕፃን ተቀብዬ ምን እመግባታለሁ



ምስለ ምቁር ወልዳ ኢየሱስ ክርስቶስ

በማለት በጣም ተጨነቀ የቤተ መቅደሱን ደወል አስደውሎ ሕዝቡ ሲሰበሰብ ስለ ድንግል ማርያም በስእለት መልክ መቅረብ አስረዳቸው ሕዝቡ በመመካከር ላይ እንዳሉ መልአኩ ፋኑኤል ኅብስት ሰማያዊ ጽዋ ሰማያዊ ይዞ ረቦ ታየ ዘካርያስ ለእርሱ የታዘዘ መስሎት ለመቀበል ቀረብ ቢል ይዞበት ወደ ላይ ከፍ አለ ሐናና ኢያቄምም ቢቀርቡ ይዞባቸው ወደ ሰማይ ወጣ ከሕዝቡ ደጋግ ናቸው የሚባሉት በየተራ ለመቀበል ቢሞክሩ ሳይሳካላቸው ቀረ ድንግል ማርያ ምን ለብቻዋ አስቀምጠው ሕዝቡ ፈቀቅ ቢሉ መልአኩ ወርዶ ከፍ አድርጎ በሰው ቁመት ልክ አንድ ክንፉን አጐናጽፎ አንድ ክንፉን ጋርዶ መግቧት ወደ ሰማይ አረገ የምግቧ ነገር ስለተያዘ ዘካርያስ በደስታ ተቀብሎ በቤተ መቅደስ እንድ ትኖር አድርጓል ።

በቤተ መቅደስ መጋረጃ እየፈተለች መሶበ ወርቅ እየሰፋች ፲፪ ዓመታት ኑራለች ከእናት አባቷ ቤት ፫ ዓመት ከቤተ መቅደስ ፲፪ ዓመት በድምሩ ፲፭ ዓመት ሲሆናት አይሁድ በምቀኝነት ተነሥተው ከቤተ መቅደሳችን ትውጣልን ብለው ከሰሷት ዘካርያስ በነገሩ ሲጨነቅ መልአከ እግዚአብሔር በራዕይ ተገልጾ ሚስቶቻቸው የሞቱባቸውን ሰዎች በትር ሰብስብና ከቤተ መቅደስ አግብተህ ስትጸልይበት እደር፣ በዚያ ላይ ምልክት አሳይሃለሁ አለው ።

ዘካርያስም እንደታዘዘው ቢያደርግ ከዮሴፍ በትር ላይ አዮሴፍ ዕቀባ ለማርያም "ዮሴፍ ሆይ ማርያምን ጠብቃት" የሚል ተጽፎ ተገኝቷል ርግብም ከራሱ ላይ አርፋበታለች ዕጣም ቢጥሉ ለእርሱ ወጥቷል በዚያም ሆነ በዚህ ለአንተ ደርሳለች ወስደህ ጠብቃት ብለው ሰጥተውታል ዮሴፍም እመቤታችን ድንግል ማርያምን ተቀብሎ ወደ ቤቱ ወስዷታል ።

እመቤታችን በዮሴፍ ቤት ስትኖር ከዕለታት አንድ ቀን እንስራዋን ተሸክማ ውሃ ለመቅዳት ወደ ወንዝ ወረደች በዚያም አንድ የተጠማ ከልብ ሲቅበዘበዝ አግኝታ ጨማዋን አውልቃ አጠጥታ መንገዷን ስትቀጥል መልአኩ ትፀንሲ (ትፀንሻለሽ) አላት ከቤቷ ደርሳ እንስራዋን ስታወርድ ደግሞ ነገራት ነገሩ ደጋገመኝ ወደ ቤተ መቅደስ ሄጄ መረዳት አለብኝ ብላ ቤተ መቅደስ ሄዳ ከደናግለ እስራኤል የተካፈለችውን ሐርና ወርቅ እያስማማች ስትፈትል መልአኩ እነሆ በድንግልና ፀነስሽ በድንግልና ትወልጃለሽ አላት እርሷም ምድር ያለ ዘር ታበቅል ዘንድ ድንግልም ያለ ወንድ ትፀንስ ዘንድ እንዴት ይቻላል እንደዚህ ያለውን የምስራች ከየት አገኘኸው አለችው ።

መልአኩም "እስመ አልቦ ነገር ዘይሰዓኖ ለእግዚአብሔር" ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር የለም ስላላት "ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ" እንደ ቃልህ ይደረግልኝ ባለችው ጊዜ ዋህድ ቃለ እግዚአብሔር በማኅፀኗ ተፀንሷል መሠረተ ሕይወት ጥንተ መድኃኒትም የተባለችው የዓለምን መድኃኒት ክርስቶስን ስላስገኘች ነው ።

እመቤታችን ድንግል ማርያም እመ ብርሃን ማኅደረ መለኮት ንግሥተ አርያም እመ ብዙኃን ተላኪተ አምላክ ወሰብእ በመሆኗ ያዘኑትን ታጽናናለች የተበሳጩትን ታረጋጋለች የከበደውን ታቀላለች የሀገራችን ሊቅ ቅዱስ ያሬድ ስለ እመቤታችን ክብር ብዙ ዝማሬን ዘምሯል ግንቦት አንድ ቀን ስለእርሷ በደረሰውም መዝሙር "ነቢያትንና ጻድቃንን ታድን ዘንድ እመ ብርሃን ተወለደች ብሏል ።

የድንግል ማርያም እናትነቷ ለተወሰኑ ሰዎች አይደለም በእግዚአብሔር ስም አምነው በቃል ኪዳኗ ለሚመጹኑ ሁሉ ምህረትን ይቅርታን ሰላምን ታሰጣለች በምድርም ሆነ በሰማይ ድኅነትን እናገኝ ዘንድ በጌታችን በመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስም አምነን በእመ ብርሃን ድንግል ማርያም ቃል ኪዳን እንማፀናለን ። ቄስ ልሣነ ወርቅ በዛብህ

# ዜና ሊቃውንት

በዛሬው የዜና ሊቃውንት አምዳችን የምናቀርብላቸሁ ስለ መልአከ ገነት ገብረ ሥላሴ ዓወቀ ነው ።መልአከ ገነት ገ/ሥላሴ ከአባታቸው ግራዝማች ዓወቀ ከእናታቸው ወ/ሮ አስካለ ሕይወት በጎጃም ሀ/ ስብከት ፍኖተ ሰላም አውራጃ ፈረስ ቤት ወረዳ እሾህ ቅዱስ ሚካኤል ከሚባለው ደብር ተወለዱ ።

ዕድሜአቸው ለትምህርት ሲደርስ በዚያው በተወለዱበት ደብር ከነበሩት መሪጌታ አፈ ወርቅ ከተባሉት መምህር ትምህርት ጀምረው ዳዊት ደግመዋል ከዚያ በኋላ ዜማ የመማር አሳብ ስለነበራቸው ደርቄ ማርያም ወደነበሩት መሪጌታ ተገኝ ሂደው ከውዳሴ ማርያም ዜማ ጀምረው የዘወትር ምዕራፍ እንዲሁም ጾመ ድጓ



መልአከ ገነት ገብረ ሥላሴ ዓወቀ ከተማሪዎቻቸው ጋር

ተምረዋል ።

ከዚያም በኋላ የቅኔ ትምህርታቸውን ለመቀጠል ከደርቄ ተነሥተው ወደ ደብረ ኤልያስ ሄደው በደብሩ ከነበሩት ሊቅ መምህር ገብረ ሥላሴ ቅኔ ተምረው ከተቀኙ በኋላ የቅኔ ትምህርታቸውን ለማጥበቅ ወደዋሸራ ማርያም ሂደው ዝነኛና ታዋቂ ከነበሩት መምህር ማዕበል ፈንቴ ዘንድ ቀደም ሲል የተማሩትን ቅኔ ከማጠናከራቸውም ሌላ አገባብና እርባ ቅምር በሚገባ አጠናቀው ተምረዋል ።

መልአከ ገነት ገብረ ሥላሴ ዓወቀ በዚህ በተማሩት ዕውቀታቸው ሳይወሰኑ ወደ በጌምድር ክፍለ ሀገር ተሻግረው ሊቦ አውራጃ ደኅማ ወረዳ ሚካኤል ደብር ከነበሩት ዝነኛና ስመጥር መምህር ጌቱ ገሞራው





www.ethiopianorthodox.org

ቀደም ሲል በተማሩት ላይ የቅኔውን ግሥ አገባቡንና እርባ ቅምሩን በሚገባ አጠናቀው ከተማሩ በኋላ በቅኔ መምህርነት ተመርቀዋል ፡

ከዚያም ቀጥሎ የቅዱሳት መጻሕፍትን ትርጓሜ ለማወቅ ባደረባቸው መንፈሳዊ ፍላጐት ከጎንደር ክፍለ ሀገር ተነሥተው ወደ አዲስ አበባ በመምጣት ከዶክተር አየለ ዓለሙ ዘንድ የመጻሕፍተ ሐዲሳን ትርጉም እየተማሩ ሳሉ ጠላት ወደ ኢትዮጵያ ሀገራችን መጥቶ ሕዝቡን እየጨፈጨፈ ሀገራችንን ስለወረራት ከአዲስ አበባ ተነሥተው እንደገና ወደ ጐጃም ሀ/ ስብከት በመሔድ ሞጣ ቅ·ጊዮርጊስ ከነበሩት አለቃ ጌታሁን የላይ ቤት የሐዲሳትን ትርጓሜ እንዲሁም የፍትሐ ነገሥትና የዳዊት ትርጓሜንም ተምረዋል ።

ለአምስት ዓመታት በተጠቀሰው ደብር እየተማሩ ከቆዩ በኋላ በእግዚአብሔር ቸርነት በአርበኞች ብርታት ጠላት ድል ተመቶ ከሀገራችን ኢትዮጵያ ከተባረረ በኋላ ለሁለተኛ ጊዜ ወደ ጎንደር ክፍለ ሀገር ሄደው በትዕይንተ ጎንደር ግምጃ ቤት ማርያም ከነበሩት መምህር ክፍሌ ይመር ዘንድ ገብተው የታች ቤት የሐዲሳትን ትርጓሜ በሚገባ ተምረዋል ።

ከዚያም በሚማሩበት ወቅት ጊዜ ወስነው ወደማታና ሌሊት ግሥ በመግሠሥ ቅኔ በመዝረፍ ብዙ ደቀ መዛሙርትን አሠልጥነው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን አበርክተዋል ።

እንደዚሁም በዚሁ ግምጃ ቤት ማርያም ከታወቁት ሊቀ መምህር ተክለ ሃይማኖት የመጻሕፍተ መነኮሳትን ትርጓሜ አሂደዋል የሐዲሳትንና የመ/ መነኮሳትን ትርጉም ተምረው ከፈጸሙ በኋላ ወደ ዶክተር አየለ ዓለሙ ሄደው [illegible] መጻሕፍት ብሉያትና መጻሕፍተ ሊቃውንትን ተምረው ለማስተማር ከሚያስችል ደረጃ ስለደረሱ ከመምህራቸው ዶ.አ.አየለ ዓለሙ የምስክር ወረቀት ተቀብለዋል ።

መልአከ ገነት ገብረ ሥላሴ ዓወቀ ራሳቸው እየተማሩ በማስተማር ብዙ ደቀ መዛሙርትን እያሠለጠኑ ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ማበርከታቸው ቢታወቅም ወንበር ዘርግተው ጉባኤ አስፍተው ቀን የመጻሕፍት ትርጉማን ማታ ቅኔን ማስተማር ከጀመሩ ፴፭ ዓመት መሆኑን ከራሳቸው ጠይቀን ተረድተናል ። በተጠቀሱት ዓመታት ስንት ደቀ መዛሙርት አሥተምረው ለቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን እንዳበረከቱ ጠይቀናቸው ሲያስረዱን ፡

ከመምህርነት ደረጃ የደረሱ ፲፯ ሲሆኑ ቅኔ እየተቀኙ የውዳሴ ማርያምና የቅዳሴ ማርያም ትርጉም እንዲሁም ከአዲሳትም ከብሉያትም ከሊቃውንትም የተቻላቸውን ያህል እየተማሩ የሚሄዱት ብዙዎች ስለሆኑ ቁጥራቸው ይህን ያህላል ብሎ ለመናገር ያዳግታል ብለዋል ።

መልአከ ገነት ገብረ ሥላሴ የሞጣ ጊዮርጊስ አለቅነት ከመምህርነት ጋር ተሰጥቷቸው ቀን የመጽሐፍ ትርጓሜን ማታ ቅኔ በመዝረፍና ግሥ በመግሠሥ ለብዙ ዓመታት ቤተ ክርስቲያንን አገልግለዋል ብዙ ደቀመዛሙርትንም አሠልጥነዋል ። በዚህም ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ደስ ይላታል ።

እኚህ ሊቅ ወደአዲስ አበባ መጥተው ከኅዳር አንድ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ወዲህ በብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ፓትርያርክ ርእሰ ሊቃነ ጳጳሳት ዘኢትዮጵያ መልካም ፈቃድ በቅዱስ ጳውሎስ መንፈሳዊ ት/ቤት እንዲያስተምሩ ተመድበው በንቃትና በትጋት በማስተማር ላይ ይገኛሉ ።

መልዓከ ገነት ገብረ ሥላሴ ዐወቀ አሉ ከሚባሉት የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት አንዱ ናቸው ብፁዕ ወቅዱስ አቡነ ተክለሃይማኖት ለአብነት መምህራን እንክብካቤ እንዲደረግላቸው መላልሰው በሰጡት መንፈሳዊ መመሪያ መሠረት አንዳንድ አህጉረ ስብከት መመሪያን ተግባራዊ ለማድረግ በመጣር ላይ ይገኛሉ ።

ቅዱስነታቸው መንፈሳዊ መመሪያ በመስጠት ብቻ ሳይወስኑ አርአያ ለመሆን ሲሉ ለመንበረ ፓትርያርክ ከተፈቀደው ፳፭ ፻ ከመቶ ሃያ አምስት ገቢ የአብነት መምህራን እንዲቀጠሩበት ስለፈቀዱ መልአከ ገነት ገ/ሥላሴ ዐወቀ ለመጀመሪያ ጊዜ ተቀጥረው በማስተማር ይገኛሉ።

እኚህ ሊቅ ቅኔ ዘርፈው ገሥሠው የመጽሐፍት ትርጓሜን አስተምረው የማይሰለቹና የማይደክሙ ስለሆኑ የመንፈሳዊ ትምህርት ፍላጐት ያላቸው ሁሉ ወደእኚህ ሊቅ እየሄዱ የፈለጉትን ለመማር ይችላሉ ።

መምህሩም ባለው ዕውቀታቸው ጠንክረው አስተምረው መልካም የሥራ ፍሬ እንደሚያሳዩ ተስፋ እናደርጋለን ።

የዜናው አቅራቢ
መ/ ክነፈ ርግብ ማርቆስ



# የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ ስለጦር መሣሪያ ቅነሳ ያስተላለፋቸው ውሳኔዎች

የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ እጅግ አሳሳቢና ውስብስብ በሆኑት በጦር ቅነሳ በሰላም ሁኔታዎች እንዲሁም ለሰላም ወዳጅ ኃይላት ሁሉ እንዲያተኩሩ እንደገና ጥሪ አደረገ ።

፩. እኛ በማህበርና በአንድነት ለሚኖሩ ሕዝብና ፍጥረት ሁሉ ስለእግዚአብሔር ሰላም እንመሰክራለን ። ይህም ራሱ በሰላምና በተስፋ እኛን ወደ ሐዲስ ሕይወት ይመራናል ። ስድስተኛው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ጉባኤ ፍትህንና ሰላምን ጠቅላላ ለሰው ልጆች መረጋጋት በክርስቶስ ክርስቲያኖች የተሰኙት ሁሉ የአብያተ ክርስቲያናት ቤተ ሰቦች እንዲሆኑ ጥሪውን አስተላልፎላቸዋል ።

፪. የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ ፡
- አብዛኛው የዓለም ሕዝብና ፍጥረት የራሳቸውን ዕድል በራስ ለመወሰን ሰብአዊ መብታቸው የተነፈገ መሆኑን ፡
- የሁለቱ መዋዕለ ነዋይና የሳይንስ ውጤቶች መሠረታዊ ከሆኑት ከሰብአዊ ፍላጐቶች ይልቅ ፍጥረተ ዓለምን ወደ እልቂት ወደ ሚመራው ዘመን አመጣሽ የጦር ትጥቅ በማመዛናቸው የዓለም ምጣኔ ሀብት መቃወሱ ፡

ከጋራ እድገትና ልማት ይልቅ በሚሊዮን የሚቆጠሩትን የሰዎች ሕይወት ጭካኔ በተመላበት መንፈስ የሚያጠፋውን የጦር ትጥቅ በመቃወም ፡

በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ሕዝቦች መሞትና መሰቃየት ምክንያት የሆነውን ጦርነትና ወታደራዊ ግጭት በአስቸኳይ እንዲቆም ፡

ከገጸ ምድር ላይ የሚግበሰበሰውን የጦር ትጥቅን ለመቃወም ለሚታገሉት ሁሉ የማያቋርጥ ድጋፍ ለመስጠት ዝግጁ መሆኑን ፡

በአሁኑ ጊዜ የሰው ልጆችን በአስጊ ሁኔታ ላይ የጣለውን የኑክሌር ጦርነትን በማውገዝ ፡ ከኑክሊር አምራች ሀገሮች ተጽዕኖ የሰው ልጅ ሕይወት ነፃ የሚሆንበት ጊዜ ቅርብ መሆኑን በመጠቆም ፡

በዓለም ላይ እጅግ አንገብጋቢ የሆነው የኑክሊር መሣሪያ ቅነሳ ተግባራዊ እንዲሆን በመግለጽ በእነዚህ ዐበይት ጉዳዮች ላይ በተለያዩ ጊዜያት ተወያይቶበታል ።

፫. በዘመናዊ መሣሪያ በመጠቀም በሰላማውያን ሕዝቦች ላይ እልቂት የሚያደርሱ ኃይላት ሁሉ በየቀኑ ፡ በየደቂቃውና በየሴኮንዱ በዓለም ላይ ለሚጠፉት የሰው ሕይወቶች ተጠያቂዎች መሆናቸውን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላው ኮሚቴ አውስቷል ።

ኑክሌር አምራች ባልሆኑት ሀገሮች የሚኖሩት ሕዝቦችና ኑክሌር



አምራች በሆኑት ሀገሮች የሚኖሩ ሕዝቦች እጅግ ለሰው ልጅ ሕይወት አጥፊ የሆኑት መሣሪያዎች እንዳይመረቱ የጋራ ግንባር ፈጥረው እንዲቃወሙ ማዕከላዊ ኮሚቴው አሳስበዋል ።

የሰላምን ገጽታ አደፍራሽ የሆነውን የኑክሊየር መሣሪያ በመቀነስና ለዚያውም የሚወጣው መዋዕለ ንዋይ ለልማትና ለማህበራዊ ኑሮ እንዲውል የዓለም ሕዝብ ከመቼውም የበለጠ እንዲያስቡ ኮሚቴው ጥሪውን አስተላልፏል ።

የሰው ልጅ በዚህ ዕድል ሳይጠቀም ይህ ዕድል ቢያመልጠው ግን የኑክሊየር መሣሪያዎች ከገጸ ምድር አልፈው ከሕዋው ላይ እንደሚገበሰበሱ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላው ኮሚቴ በአንክሮ ጠቁሞታል ።

የአሜሪካው ፕሬዚዳንት ሬገንና የሶቪየት ሕብረት ዋና ፀሐፊ ሚካኤል ጎርባቾቭ በአይስላንድ ርዕሰ ከተማ በሆነችው ሬክጃቪክ ተገናኝተው ስለጦር ቅነሳና ስለሁለቱ ሀገሮች በሚመለከት መሠረተ ሐሳብ ላይ በሚወያዩበት ጊዜ በሁለቱ መሪዎች መካከል ይታይ የነበረው መግባባት በሰላም ላይ የተመሠረተ እንደነበር የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላው ኮሚቴ አውስቶታል ።

የኑክሊየር መሣሪያዎችን መቀነስ የሚቻልም መሆኑንና እንዲሁም ከገጸ ምድር ላይ የኑክሌር መሣሪያ አሽቅድድምን ለማስወገዱ ወይም ለማቆም በስብሰባው ጊዜ መረጋገጡን ማዕከላዊ ኮሚቴው በታላቅ ደስታ አብሥሮታል ። ሁለቱም መሪዎች ስለዘመናዊ መሣሪያዎች ቅነሳ ከስምምነት ላይ መድረሳቸውን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ ጠቁሞታል ።

በስብሰባውም ጊዜ የሁለቱ መሪ

www.ethiopianorthodox.org

… ውይይት የተለየ ትኩረት የሰጠው በዓለም በሚደረገው የኑክሊየር መሣሪያን በሚመለከት አሳሳቢ ጉዳይ ላይ እንደነበረም ማዕከላዊ ኮሚቴው ገልጾታል ።

ከዩናይትድ እስቴት አሜሪካ በቀረበው የመከላከያ ኃይል ዕቅድ (ፕላን) ላይ በጣም አለመግባባት እንደነበረ ኮሚቴው አረጋግጧል ።

የኑክሊየር መሣሪያዎችን ከዓለም ላይ ፈጽሞ ለማስወገድ እንዲቻል የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ ፡

— የኑክሊየር መሣሪያን ቅነሳ ከግቡ ለማድረስና የኑክሊየር ሙከራን ለማቆም የተደረገ የጋራ ውይይትም በእውነት ላይ የተመረኰዘ ስለነበር ከሁለቱ በኩል አጥጋቢ ውጤት የኑክሊየር መሣሪያዎችን በግፍ ከማምረት እንዲቆጠቡና ለዚህም የሚወጣው የጥሬ ሀብት እንዲቀነስ ፤

— ጠቅላላ የፕሮግራሙ ቅርጽ የኑክሌር መሣሪያዎችና እንዲሁም ማጠራቀሚያዎች ጭምር በተሻሻለና በተመጣጠነ ሁኔታ የቅነሳ እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ ጥሪ አድርጓል ።

ጠቅላላ የኑክሊየር ሙከራዎችን ወደ ፍጻሜ ለማድረስ ዛሬ አንገብጋቢና አስፈላጊ መሆኑንም ኮሚቴው አምኖበታል ፡

የዓለምን ፀጥታዎች ወደ ከፋ ደረጃ የሚመሩትን የኑክሌር መሣሪያዎች ሙከራ በማቆም በዓይነትና በብዛት ከማምረት እንዲከስሙና በተጨማሪም የጦር ትጥቅን ለመቀነስ ዓይነተኛ ተግባር እንዲሆን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ እምነቱ ነው ።

የኑክሊየር መሣሪያዎችን በብዛት ማግበስበስና ማምረትን አጥብቆ መከላከል በጣም አስፈላጊ መሆኑን ጭምር ኮሚቴው አስገንዝቦታል ።

ሁለቱም የዩናይትድ እስቴት አሜሪካና ሶቪዬት ሕብረት የኑክሊየር ባለቤቶች እንደመሆናቸው መጠን የኑክሌር ቅነሳን በሚመለከት ሂደት ላይና በየጊዜው ለሚያደርጓቸው ሙከራዎች ሁሉ የተለየ ኃላፊነት እንዳለባቸው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ አስገንዝቦታል ።

ሶቪየት ሕብረት የሙከራውን ጊዜ ለ ፲፰ ወራት ያህል እንዲዘገይ ሙሉ በሙሉ ፈቃደኛ በመሆን ተቀብላ እንደነበረች ማዕከላዊው ኮሚቴ ገምግሞታል ።

የፈረንሳይ መንግሥት ግን ለጊዜው እንዲቆም የተወሰነውን ውሳኔ ባለማክበርና በዓለም አቀፍ ላይ የተመረኰዘውን የሙከራ ማቆም ስምምነት በመጣስ በፓስፊክ ውቅያኖስ ውስጥ የኑክሌር ሙከራን የቀጠለች መሆኑን ኮሚቴው በጽሙና ሊገነዘብ ችሏል ።

የኑክሌር መሣሪያ ሙከራዎች በአስቸኳይ ዛሬውኑ ካልቆሙ በቀር ነገ የኑክሌር መሣሪያዎች ባለቤት የሚሆን ሌላ አዲስ ትውልድ የሚፈጥር መሆኑን የዐለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ አመልክቷል ።

ይህ አሳሳቢ ሁኔታም ጠቅላላ የዓለም ሕብረተሰብን የሚመለከት መሆኑን ጭምር ማዕከላዊ ኮሚቴው ጠቁሞታል ።

ይህንን የተገነዘቡ ሀገሮች ፡

፩. አርጀንቲና ፪. ሜክሲኮ ፫. ግሪክ ፬. ስዊድን ፭. ሕንድ ፮. ታንጋኒካ መሆናቸውን ማዕከላዊ ኮሚቴው ገምግሞታል ።

በእነዚህ ሀገሮች የሚኖሩ ሕብረተሰቦች የኑክሌር ቅነሳን በሚመለከት ጉዳዮች ላይ ሰፊ ዓለም አቀፋዊ ውይይት ማድረጋቸውን የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ ጠቅሶታል ። እነርሱም በየጊዜው በዓለም ዙሪያ ለሚደረገው የኑክሌር ሙከራ በቂ ማስረጃዎችን በመያዝ የዚህ ዓይነት አስጊ ተግባር በዓለም ዙሪያ እንዳይቀጥል መወሰናቸውን ማዕከላዊ ኮሚቴው ተገንዝቦታል ።

፮. ደግሞ ሌሎች የተስፋ ምልክቶች አሉ የብዙ ንቅናቄዎች ጥረት ፤ የአብያተ ክርስቲያናት፣ የወጣቶችና የሴቶች ንቅናቄዎች ፤ የመንግሥታት ዓይነተኛ ተቃውሞ፣ እንደኒዘርላንድ የኑክሌር መሣሪያ ተቃውሞና እንደ ደቡብ ፓስፊክ አህጉር አቀፍ ከኑክሌር ነፃ የመሆን ስምምነት ጉባኤ እጅግ የሚያበረታቱ ናቸው ።

እንደ አውሮፓ አቆጣጠር ጥር ፲፱፻፹፯ ዓ.ም. የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ ስብሰባ ዋዜማ ዩናይትድ እስቴት አሜሪካና ሶቪየት ሕብረት ስለኑክሌርና ስለእስፔስ (ስለህዋ) መሣሪያዎች በጄኔቭ ውስጥ የጋራ ውይይቶችና ተጨባጭ ውሳኔዎች ወይም እርምጃዎች የተሻለ ውጤት እንደሚያሳይ ማዕከላዊ ኮሚቴው አምኖበታል ።

፯. የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ኮሚቴ ዓለም አቀፋዊ ውይይቶች በሚቀጠሉበት ወቅት — ለወደፊት ጠቅላላ የኑክሌር ሙከራን ለማቆም ስምምነት እስኪ ደረሰ ድረስ ስለኑክሌር ሙከራዎች ጊዜያዊ ገደብ እንዲደረግ በይፋ ወይም በግልፅ እንዲናገሩ ለተወሰነ ጊዜ እስትራቴጂክ መሣሪያዎችን መቀነስና እንዲሁም መፈንዳትን ማስወገድን በሚመለከቱት ነጥቦች ላይ ከስምምነት ላይ እንዲያደርሱ የእስፔስ (የህዋው) መሣሪያዎችን ማሳደግ ወይም መጨመር እንዲሁም ለሰው ሕይወት ተጻራሪ የሆኑትን የፍንዳታ ሙከራዎች ከማጠንከር በመቆጠብ ወይም በማስወገድ ጠቅላላ አስፈላጊ እርምጃዎችን እንዲወስዱ ለሁለቱም መንግሥታት ቃለ መጠይቅ አስተላልፎላቸዋል ።

፰. የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ የሶቪየት ሕብረት መንግሥት ለኑክሌር መሣሪያ ሙከራዎች የጊዜ ገደብ እንዲኖረው ለጠየቀው የስምምነት ጥያቄ ተጻራሪ ያልሆነ መልስ እንዲመልስ በተለይ የአሜሪካን መንግሥት ጠይቋል ።

፱. የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ በፖሊዚያ የሚደረገውን የኑክሌር መሣሪያ ሙከራ ለወደፊት እንዲያቆም ለፈረንሳይ መንግሥት ጥያቄ አቅርቦለታል ።

፲. ኑክሌር በሌለው አካባቢና እንዲሁም ከኑክሌርና ከጋራ ኃይሎች መካከል በአለው ክፍል ስለመሣሪያ አስተያየታዊ ውይይት እንዲኖረው የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ በተለይም በሁለቱ ወታደራዊ ቃል ኪዳኖች ማለትም ስለጋራ የጦር መሣሪያዎችና ስለግበረ ኃይላት ቃል ኪዳን በአላቸው በኔቶና በዋርሶው መካከል ውይይቶች እንዲካሄዱ አጥብቆ አሳስቦአቸዋል።

፲፩. የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ ስለሰላም ለሚያደርጉት ጥረት በቅድሚያ በአስቸኳይ ስለዚህ ተግባር የተለየ ትኩረትና ክትትል እንዲያደርጉ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት አባላትን ሰደሚል ።

ከእነርሱም አያሌዎቹ ወይም አብዛኞቹ በትምህርታዊ መስኮች በሕዝባዊ አገልግሎቶች ላይ በመሳተፍ በእነዚህ ተግባሮች ላይ ግልጽ አቋም አስቀድመው ወስደዋል ።

ከእነርሱም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ ክርስቲያኖች ሁሉ፡

የኑክሌር ሙከራ አስቀድሞ የሚያከትምበትን የተለየ ሥራ በመቀየስ ጊዜአቸውን ለዚህ በማዋል ፡

የጋራ መተሳሰብንና የጋራ ዕቅድን ለማሳደግ ወይም ከፍ ለማድረግ በአብያተ ክርስቲያናት መካከል ከመልካም አመለካከት ጋር የሁለገባዊ ውይይት በማሳደግ ስለሕዝባዊ ትምህርትና ውጤቶች ከመንግሥታትና ከመንግሥት አካላት ጋር የሚያዋህዱ ሌሎች የሰላም ኃይሎችን በማገናኘት ፡

ሀገሮች ስለደቡብ ፓስፊክ የወሰዱትን ሕጋዊ እርምጃ በመደገፍ በሰላም በፍትህ ላይ በተመሠረተ ኑሮ እንዲኖር የዓለም ሕብረተሰብ በትምህርት በመገንባት ራሳቸውን ለመሥዋዕትነት በመሥጠት ስለሕዝቡ ከልብ በመነጨ ጸሎት በመጠመድ ስለፍትህ ፡ ስለሰላምና ስለጠቅላላ የሰው ልጆች ኃይላቸውን እንዲያጠናክሩ በእነዚህ ተግባሮች ላይ ጥሪ አድረገላቸው ።

፲፪. የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ማዕከላዊ ኮሚቴ ዓላማዎችን በመጠበቅ እርምጃዎችን ወደ ተግባራዊነት ለወሰዱት የአብያተ ክርስቲያናት ገጽታዎችንና ሁኔታዎችን በማጤን ይህን ውሳኔ በሚመለከት ከአባላት አብያተ ክርስቲያናት ጋር ዜና (ኢንፎርሜሽን) እንዲለዋወጥ የዓለም አብያተ ክርስቲያናት ዋና ጸሐፊውን በመጨረሻ ጠይቋል ።

ቄስ እያሱ ገብሬ

# ልማት በቤተ ክርስቲያን

ዛሬ የምናቀርበው ልማት በቤተ ክርስቲያን ጽሑፋችን በሸዋ ሀ/ስብከት ብመርሐ ቤቴ አውራጃ ውስጥ ስለሚገኘው ልማት ነው በዚህ አውራጃ ፪፻፲፬ አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ እነዚህም ፩ኛ/ ቅዱስ አማኑኤል ፪ኛ/ ቅዱስ ገብርኤል ፫ኛ/ ቅዱስ ጊዮርጊስ ናቸው በዓለም ከተማ የቆፍና አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ቀደምትነት አላቸው ከሚባሉት አብያተ ክርስቲያናት አንዱ ነው ምክንያቱም ይህ ቤተ ክርስቲያን በእነ አብርሃ ወአጽብሐ ዘመነ መንግሥት የተተከለ መሆኑ ተገልጾልናል በዚሁ አካባቢ ያሉትም ሽማግሌዎች ነግረውናል ። የቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን በጥንታውያን ታላላቅ ወይራዎችና ጥዶች እንዲሁም በባሕር ዛፍ የተከበበ ሲሆን ጸድቀው ለምልመው ይገኛሉ ። በዚሁም በቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ምን አይነት ልማት መኖሩን ሊቀ ትጉሃን ጌታቸው ኃይሌ የመርሐ ቤቴ አውራጃ ሊቀ ካህናት ጠይቀናቸው ነበር ትንሣኤ በዚህ በቅዱስ አማኑኤል ቅጽር ግቢ ብዙ ጥንታውያን ዛፎች ይታያሉ ነገር ግን የማያረጅ የለምና ይህንን ዛፍ የሚከተሉ ሌሎች የተከላችኋቸው ዛፎች እንዳሉ ቢገልጹልን።





www.ethiopianorthodox.org

መልስ ምእመናን በመተባበር አሁንም በብዛት የተተከሉ ዛፎች አሉ እነዚህም ፲፯ሺ ያህል ጥዶች ተተክለው ነበር ነገር ግን ከተተከሉት ፲፯ሺ ጥዶች የደረቁት ደርቀው ከእነሱ ፲ሺ ጸድቀው ይገኛሉ ይህ ብቻ ሳይሆን ባሕር ዛፎችም ከ፲፰ሺ ያላነሱ ተተክለው እነሆ በልምላሜ አሸብርቀው ይታያሉ ።

ትንሣኤ. እነዚህ ወይራዎች የተተከሉበት ዘመን ይታወቅ ይሆን

መልስ ከሽማግሌዎች ጠይቀን እንደተረዳነው እነዚህ ወይራዎችና ጥዶች ከ፪፻ ዓመት በላይ ዕድሜ እንዳላቸው ይነግሩናል ።

ትንሣኤ. በዚህ በቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን ይህ ብቻ ነው ወይስ ሌላ ልማት አለ?

መልስ ሌሎችም ብዙ ልማቶች አሉን ለምሳሌ እርሻ ት ቤት የመሳሰሉት ልማቶች አሉን በቤተ ክርስቲያኑ አካባቢ እርሰን የጤፍን ዘር ዘርተን ፰ ኩንታል ያህል አግኝተንበታል ያገኘነውንም ምርት እየሸጥን ገንዘቡን በባንክ እናስገባዋለን ይኸውም በባንክ ተቀምጦ እንዲኖር ሳይሆን የጎጆ ኢንዱስትሪ ለማቋቋም ሐሳብ ስላለን ለዚህ ለምናቋቁመው እንዱስትሪ መነሻ ይሆናል በሚል ሐሳብ ነው ።

ትንሣኤ. ከዚህስ በፊት በእርሻ ትጠቀሙ ነበር አሁንስ ያ በእርሻ ትጠቀሙበት የነበረው ማሳ አለ ወይ?

መልስ አለ አሁንም በእርሻ እየተጠቀምንበት ነው እንዲያውም ዛሬ ፲፱፻፸፱ ዓ/ም ፫ ጥማድ ያህል የዋለበት ማሽላ ዘርተን ፍሬውን በመጠባበቅ ላይ ነን።

ትንሣኤ. እርሻውን የሚያርሰው ማን ነው ?

መልስ እርሻውን የሚያርሱልን ምእመናን ናቸው

በትምህርት ቤትም በኩል ስላለው ልማት ሊቀ ትጉሀን ጌታቸው ኃይሉ ሲገልጹ በዚህ በቅዱስ አማኑኤል ቤተ ክርስቲያን :

፩. የቅኔ መምህር

፪. የዝማሬና የመዋሥዕት መምህር

፫. የንባብ

፬. ከጐንደር በዓታ ተመርቀው የመጡ የአቋቋም መምህራን በጠቅላላ ፫ መምህራን አሉ ብሏል

ትንሣኤ. ባሁኑ ጊዜ መምህራንም ቢገኙ በአንዳንዱ ቦታ ተማሮች አይገኙም ይባላል ግን በዚህ ቤተ ክርስቲያን ምን ያህል ተማሮች ይገኛሉ ።?

መልስ የንባብ ከመቶ የማያንሱ አሉ የአቋቋም ተማሮችም ፳ የሚሆኑ ይገኛሉ እንደዚሁም የቅኔም ሆነ የዝማሬ መዋሥዕት አሉ።

ትንሣኤ መምህራኑ ደመወዝ ያገኛሉ ወይስ በነጻ ነው የሚያስተምሩ ?

መልስ መምህራኑ ለጊዜው ቅዋሚ በጀት የላቸውም ከሰበካ ጉባኤ ድጎማ እየተደረገላቸው ናቸው ይሁን እንጂ ለወደፊት ደመወዝ እንዲያገኙ ተስፋ ሰጥተናቸዋል በድጎማ የሚኖሩበት ጊዜ ረጅም አይሆንም ብለዋል።

ልማት ከጥንት ከመጀመሪያው ሰው ተያይዞ የመጣ እንጂ ለሰው ልጆች እንግዳ ነገር አይደለም የመጀመሪያው ሰው ከተፈጠረ በኋላ በሥራ ፈትነት የዋለበት ቀን ከቶ እንዳልነበረ ታሪክ ያስታውሰናል ።

# ግበሩ በዓለ በትፍሥሕት/በዓልን በደስታ አክብሩ

ይህንን ትንቢታዊ ቃል የተናገረው ነቢዩ ዳዊት ሲሆን እርሱ ለነበረበት ዘመን ሳይሆን ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ተሰቅሎ ሙቶ ተነሥቶ ዓለምን አድኖ ከዐረገ በኋላ ምዕመናን የተደረገላቸውን የቸርነቱን ሥራ እያሰቡ በዓሉን በደስታ የሚያከብሩ መሆናቸው ስለ ተገለጸለት ነው ። ይኸውም እግዚአብሔር እግዚእ አስተርአየ ለነ ግበሩ በዓለ በትፍሥሕት ጌታ እግዚአብሔር ለእኛ ተገለጸልን በማለቱ ታውቆአል ።

ይህም የትንቢት ቃል ከተፈጸመ በኋላ ሐዋርያት ከመንፈስ ቅዱስ ተረድተው የጌታን ዘጠኙን በዓላት በዓመት አንዳንድ ጊዜ ብቻ እንደ ዕለተ ሰንበት እንዲከበሩ አዘዙ ከዚያን ጊዜም ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ በክርስቲያኖች ዘንድ ይከበራሉ ። በዓላቱም

፩ኛ/ መጋቢት ፳፱ ቀን ጌታችን የተፀነሰበት

፪ኛ ልደት

፫ኛ ጥምቀት

፬ኛ ልደተ ሰምዖን

፭ኛ መጋቢት 27 ቀን ስቅለቱ

፮ኛ ትንሣኤ

፯ኛ ዕርገት

፰ኛ መንፈስ ቅዱስ የወረደበት በዓለ ሐምሳ ጰራቅሊጦስ

፱ኛ ደብረ ታቦር ናቸው ።

በዚህ ጽሑፍ ግን ለመግለጽ የፈለግነው ስለ በዓለ ዕርገት ነው በዓለ ዕርገት እንደ ዕለተ ሰንበት ሆኖ እንዲከበር ታዝዟል የአከባበሩንም ሁኔታ ከእግዚአብሔር ቃል መረዳት ይቻላል ቃሉም ይህ ነው ። ፈቃድህን በተቀደሰው ቀኔ ከማድረግ እግርህንም ከሰንበት ብትመልስ ፡ ሰንበትንም ደስታ እግዚአብሔርም የቀደሰውን ክቡር ብትለው የገዛ መንገድህንም ከማድረግ ፈቃድህንም ከማግኘት ከንቱ ነገርንም ከመናገር ተከልክለህ ብታከብረው በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ደስ ይልሃል ።

በምድርም ከፍታዎች ላይ አወጣሃለሁ ፡ የአባትህንም የያዕቆብን ርስት አበላሃለሁ ። የእግዚአብሔር አፍ ተናግሮአልና ይላል ኢሳ ፶፰ ከዚህ ላይ የበዓል ነገር ሲነሣ አንዳንድ ሰዎች "የሰነፍ ሰው በዓሉ ብዙ ነው" ካህናት የእግዚአብሔርን በዓል አክብሩ የሚሉት ሥራ ስለሚጠሉና ሰዎችን ከችግር ላይ ለመጣል ነው እያሉ ይናገራሉ ። በዓል እንዲከበር የአዘዘ እግዚአብሔር መሆኑን ገልጾአል ። የአባትህን የያዕቆብን ርስት አበላሃለሁ ። አለ እንጂ እስርብሃለሁ ወይም ችግርን አመጣብሃለሁ አላለምና ሰዎች ከክፉ ነገር ተከልክለው በዓሉን በደስታ ቢያከብሩ መልካም ነው ።

ስለመድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ዕርገትም የሚናገሩ መጻሕፍት ብዙ ናቸው ፤ ከእነርሱም ጥቂቶችን ለማስረጃ መጥቀስ ካስፈለገ ዳዊት እግዚአብሔር በምስጋና ዓረገ ጌታችንም በቃለ ቀርን አምላካችን አመስግኑ ብሎአል ። መዝሙር ፵፮ እንዲሁም የጻድቃንን ዕርገት ያስብ ዘንድ መቅድመ ወንጌል ።

ጌታ ኢየሱስም ከእነርሱ ጋር ከተናገረ በኋላ ወደሰማይ ዐረገ በእግዚአብሔርም ቀኝ ተቀመጠ ማር ፲፮.፲፱ እስከቢታንያም አወጣቸው እጆቹንም አንስቶ ባረካቸው ሲባርካቸውም ከእነርሱ ተለየ ወደ ሰማይም ዐረገ ሉቃ ም ፳፬.፶ ፶፩ ።

ይህንንም ከተናገረ በኋላ እነርሱ እያዩት ከፍ ከፍ አለ ። ደመናም ከዓይናቸው ሰውራ ተቀበለችው እርሱም ሲሄድ ወደ ሰማይ ትኩር ብለው ሲመለከቱ ሳሉ እነሆ ነጫጭ ልብስ የለበሱ ሁለት ሰዎች በአጠገባቸው ቆሙ ። ደግሞም የገሊላ ሰዎች ሆይ ወደሰማይ እየተመለከታችሁ ስለ ምን ቆማችሁ? ይህ ከእናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል ። አሉአቸው ይላል ።

እንዲሁም በሥጋ የተገለጠ በመንፈስ የጸደቀ ለመላእክት የታየ በአሕዛብ የተሰበከ በዓለም የታመነ በክብሩ ያረገ የክብር ባለቤት ኢየሱስ ክርስቶስ እንደሆነ ተጽፎ ይገኛል ፩ኛ ጢሞ ም ፫ ፲፮ ሊቀ አፈወርቅ ዮሐንስም አርባ ስድስተኛውን መዝሙር በተረጐመበት የምርመራ መጽሐፍ ድል መንሣት ባለበት የነጋሪት ድምፅ እግዚአብሔር ዐረገ ብሏል ። እርሱ ዐረገ አለ እንጂ መላእክት አሳረጉት አላለም ። በፊቱም መንገድ የሚመራ አላስፈለገውም በሥልጣኑ ዐረገ እንጂ ኤልያስ እንደ ክርስቶስ ሊያርግ አልቻለም ። መላእክት ወደታዘዙበት ቦታ ወሰዱት እንጂ ፡

ስለዚህም ወንጌላዊው ሉቃስ የሐዋርያትን ሥራ በሚናገር መጽሐፉ ወደሰማይ ሲያርግ ደቀ መዛሙርቱ ወደእርሱ አቅንተው ያዩ እንደነበር ተናግሯል ይሁን እንጂ መላክት አሳረጉት ወይም ተሸከሙት አላለም ። ያረገበት ቦታ ገንዘቡ ነውና ሕመም የሚሰማው ግዙፍ ሥጋን ተዋሕዶ ሳለ በተነሣ በአርባ ቀኑ ደቀ መዛሙርቱ እያዩት አርጓል ያረገበትንም ዕለት በማስታወስ ቤተ ክርስቲያናችን ታከብረዋለች ።

መ/ ይባቢ. መልአከሀ

እግዚአብሔር አዳምን ከፈጠረው በኋላ ቁጭ ብለህ ብላ አላለውም በኤድን ገነት ተከለ ያችንም ገነት ይጠብቃትና ይኮተኩታት ዘንድ ከዚያች አስቀመጠው ሲል ቅዱስ መጽሐፍ ያረጋግጣል ። ዘፍ ፪.፲፭

ይህንንም አብነት በማድረግ ያ ከመጀመሪያው ሰው ተያይዞ የመጣው አምላካዊ ትእዛዝ እነሆ ዛሬም ይሠራበታል ስለዚህ ልማት የሚገኘውም ችግር መድኃኒት ነውና በተቻለን መጠን ልማትን እንውደድ ጓዶችንን እናልማ ።

ከንፈርግብ ማርቆስ





www.ethiopianorthodox.org

# የእግዚአብሔርን ቸርነት ተናገሩ

እግዚአብሔር አምላካችን ቸርነቱን ለሰው የሚገልጥባቸው የተለያዩ መንገዶች አሉ የእርሱን ቸርነት መግለጫ መንገዶች አንድ በአንድ ዘርዝሮ በጽሑፍ ለማስፈር አይቻልም ቢሆንም ለማስረጃ ያህል መጥቀሱ አስፈላጊ ነው ።

· የእግዚአብሔር ቸርነት ከሚገለጽባቸው ክብዙዎቹ አንዱ በፀበሎች አማካይነት በሕሙማን ላይ የሚገለጸው አምላካዊ ፈውስ ነው ። ለተወሰነ ዘመን በዓለም ላይ የሚኖር ሰው ሁሉ መዋዕለ ሕይወቱን በመላ በተድላና በደስታ ለማሳለፍ አይችልም ኃዘንና ደስታ ጥጋብና ረኃብ ይፈራረቁበታል ።



ብፁዕ አቡነ ሰላማ ለሕሙማኑ ትምህርት ሲሰጡ

አንዳንድ ጊዜ በረኃብና በጽምዕ ሲፈተን ሌላ ጊዜ በደዌና በመሳሰሉት ይፈተናል ። የሚደርስበትን ፈተና ሁሉ ለመወጣት የሚችለውም በገዛ ኃይሉ ብቻ ሳይሆን በእግዚአብሔር አጋዥነትና ቸርነት ነው ከእግዚአብሔርም ቸርነት በጎነት አንዱ በፀበል ሚገኘው ፈውስ ነው ።

የፀበል ፈውስ የተጀመረው በዘመነ ሐዲስ አይደለም በዘመነ ብሉይም የነበረ አሁንም ያለ ወደፊትም ያለማቋረጥ የሚቀጥል መሆኑ የሚያጠራጥር አይደለም ለማስረጃ ይሆነን ዘንድ ከመጽሐፍ ቅዱስ በፀበል የዳኑትን እንጥቀስ ።

ጻድቁ ኢዮብ የሚቆማምጥ በሽታ ይዞት ነበር ከመላ ሰውነቱ ክፍል ምንም ሳይቀር ተቆማመጠ ይህም ደዌ ለፈተና የመጣ መሆኑን ኢዮብ ተገንዝቦ በትዕግሥት ተቀበለው እግዚአብሔር የኢዮብን ትዕግሥት ተመልክቶ ወደ ዮርዳኖስ ውሀ ሄዶ እንዲታጠብ አዘዘው እርሱም ሄዶ በዮርዳኖስ ውሃ በተጠመቀ ጊዜ ከደዌው ከመፈወሱም ሌላ የተቆራረጠውም አካሉ እንደቀድሞው ተመልሶለታል ።

እንደዚሁም ንዕማን የሚባል የሶርያ መስፍን በለምፅ በሽታ ተለክፎ ሲሠቃይ ከቶየ በኋላ ነቢዩ ኤልሣዕ ንዕማንን ወደ ዮርዳኖስ ውሀ ሂዶ እንዲጠመቅ አዘዘው እርሱም የነቢዩን ቃል በመስማት ሂዶ በዮርዳኖስ ውሀ ቢጠመቅ ካለበት የለምጽ በሽታ ወዲያውኑ ተፈውሷል ፪ኛ /ነገ.፭.፲፬ ።

ለማስረጃ ያህል እነዚህን ጠቀስን እንጂ በዘመነ ብሉይ በፀበል ተጠምቀው የዳኑት እነዚህ ብቻ አይደሉም ወደዘመነ ሐዲስ መለስ ብለን ስንመለከትም ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሰው ሆኖ ሥጋን ለብሶ ያስተምርበት በነበረው ወቅት ከእናቱ ማኅፀን ዕውር ሆኖ የተወለደ አንድ በሽተኛ ሰው ነበር ። አይሁድ ስለዚህ በሽተኛ የተለያየ አመለካከት ነበራቸው አንዳንዱ በወላጆቹ ኃጢአት ነው ሲሉ ሌሎች ደግሞ በራሱ ኃጢአት ነው ይሉ ነበር ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ጭቃውን እንደ ሥዕል ነድፎ በግንባሩ ላይ አደረገና ሂደህ ሰሊሆም በተባለው ፈሳሽ ውሀ ተጠመቅ ታጠብ አለው ሂዶ ታጥቦ አየየ ተመልሷል ዮሐ ፱.፩ ፍ.ም ።

በተጨማሪም በኢየሩሳሌም ቤተ ሳይዳ በምትባል የበጐች መዋኛ ነበረች በዙሪያዋ ዕርከን ነበረባት በየሳምንቱ ቅዳሜ መልአክ ከሰማይ ወርዶ ውሀውን ባነዋወጠው ጊዜ በመጀመሪያ ደርሶ የተጠመቀው ሰው ይድን ነበር ይህንን ፈውስ ለማግኘት በዚያ አካባቢ ከተሰበሰቡት መካከል የ፴፰ ዓመት በሽተኛ ነበር ጌታችንም ይህንን በሽተኛ ፈውሶታል ። ዮሐ ፭.፩

በውሀ ታጥቦና ተጠምቆ መፈወስ እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሀ ፈሳሽ ሳይሆን ከጥንት ሲያያዝ የመጣ መሆኑን በዚህ ለመረዳት ይቻላል ።

በዘመናችንም የሐመረ ኖኅ ኪዳነ ምሕረትን የቡልቡላ አቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስን የአቃቂ ደብረ ከዋክብት አቡነ አረጋዊንና ገብረ ክርስቶስን ጸበል ከአዲስ አበባ ከተማም ወጣ ብለን የደብረ ሊባኖስን የሚጣቅ አማኑኤልን በጎንደር ሀ/ስብከት የሰጥላ ማርያምን የገንተኛ ቅ/ሚካኤልን ወዘተ እንዲሁም ወደ ባሌ ሀ/ስብከት መለስ ብለን በቅርቡ ተከሥቶ የሚሰጠውን ፈውስ ስንመለከት የእግዚአብሔርን ቸርነት እንድንመሰክር በመንፈስ እንገደዳለን ።

ምንም በየአህጉረ ስብከቱ በፈዋሽነታቸው የታወቁ ጸበሎች መኖራቸው ቢታወቅም በዚህ ጽሑፍ ለአንባብያን ለመግለጽ የፈለግነው በባሌ ሀ/ስብከት በጐባ ከተማ በደብረ ታቦር ሥላሴ አጥቢያ ስለሚገኘው ጸበል ነው ።

ጸበሉ የሚገኘው ከዋናው ከተማ በስተሰሜን ነው ስለጸበሉ ሁኔታ አንዳንድ አዛውንቶችን አነጋገርናል ጸበሉ የእግዚአብሔር ፈቃዱ ሆኖ አሁን ተገለጸ እንጂ ቀድሞም ነበር ብዙ ድውያንም እየተጠመቁና እየጠጡ ይፈወሱበት ነበር ነገር ግን መሬቱ የአንድ ግለሰብ ስለነበር በመሬቱ ላይ ማንም ሰው ሊያልፍ አይችልም ብሎ ስለከለከለ ተሠውሮ ኑሯል። አንዳንድ የሚያውቁ ሰዎች ሌሊት እየሄዱ በመጠጣትና በመጠመቅ ካለባቸው ደዌ ይፈወሱ ነበር ።

አሁን ግን መሬት የመንግሥት ስለሆነ ይኸውና ሁሉም በሽተኛ ከበሽታው እየተፈወሰበት ነው ብለውናል ።

ብፁዕ አቡነ ሰላም የባሌ ሀ/ስብከት ሊቀ ጳጳስ በሽተኞችን በማስተማርና በማጥመቅ በማጽናናት ጢትና ማታ አይለዩም ለበሽተኞች መጠለያ ይሆን ዘንድ የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ለችግረኞች የለገሰው ድንኳን ተዘርግቷል በአንድ ድንኳን ደግሞ የጻድቁ አቡነ ተክለ ሃይማኖት ጽላት ገብቶ በየሳምንቱና በወር የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ዕለት እየተቀደሰ ከበሽታቸው የተገላገሉት ሰዎች የክርስቶስን ሥጋና ደም ይቀበላሉ ።

ብፁዕ አቡነ ሰላማም መዋዕለ ጾሙን ያሳለፉት በዚያው ድንኳን ሌሊት ሰዓታት በመቆም ቀን በመጸለይና በማስተማር መሆኑ ተገልጿል ሕሙማኑን የሚያጠምቁ ፬ መነኮሳት ተመድበው ፪ ከሰዓት በፊት ፪ ከሰዓት በኋላ ይጠምቃሉ ።

በፀበሉ አካባቢ በሽታ ከሚያስታያቸው በስተቀር ጸጥታ የሰፈነ ነው በጥምቀት ጊዜ እንዳይሸቀዳደሙ ፬ እንጨቶች ተተክለው በእንጨቶቹ አንጻር ጸበሉን የያዙት ዕቃዎች ይደረደሩና በቅደም ተከተላቸው መጠመቅ እንጂ እኔ እቀድም እኔ እቀድም በማለት መጋፋት የለም ።

ጠበሉቹ የእግዚአብሔር አብ የሥላሴ የመድኃኔ ዓለም የቅዱስ ሚካኤል የቅዱስ ገብርኤል የኪዳነ ምህረት የአቡነ ተክለ ሃይማኖት ሲሆኑ ማንኛውም በሽተኛ ይፈወሳል ።

የጸበሉ ዙሪያ ንጽሕናው የተጠበቀ እንዲሆን ተብሎ በአንድ ጊዜ ከ፲፭ ሰው በላይ ለማስተናገድ የሚችል ሽንት ቤት በመቆፈር ላይ ይገኛል ። በሽተኞች ከበሽታቸው ተፈውሰው እስከሚመለሱ ድረስ እንዳይቸገሩ በማለት ከመጠለያው ድንኳን አጠገብ የላመ የጣመ ምግብ ሳይሆን ሻሂና ዳቦ በክክና በሽሮ ወጥ እንጀራ ቤተ ክህነቱ እያዘጋጀ ያቀርባል ።

በባሌ ሀ/ስብከት በጐባ ከተማ አካባቢ በደብረ ታቦር ሥላሴ አጥቢያ በቅርቡ ተከሥቶ ሥራውን በማስፋፋት ላይ የሚገኘው ጸበል በአሁኑ ጊዜ ይህንን የመሰለ ይዞታ ያለው መሆኑን በአገራችን ሂደን በዓይናችን ተመልክተናል ።

ወይ ገጽ ጽ፻ ዞሯል

# የእየላ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

ታሪካዊው የእየላ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የሚገኘው በወሎ ክፍለ ሀገር በላስታ አውራጃ ግዳን ወረዳ የተከዜ ወንዝ ምንጭ ከፈለቀበት አጠገብ ነው ።

ቀዳማዊ ምኒልክ ከአክሱም ተነሥቶ የኢትዮጵያን ታሪካዊ ቦታዎችን እየተዘዋወረ ለመጐብኘት በተነሣ ዘመን የአሪቱን ሊቀ ካህናት አዛርያስን ታቦተ ሚካኤልን አስይዞ ጉዞ በማድረግ ዛሬ የእየላ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ መቅደስ ከሚገኝበት አጠገብ ደብስ ከሚባል ቦታ ሲደርስ ድንኳን አስተክሎ ዕረፍት እንዳደረገ በጸና ታመመ ሠራዊቱም አዘኑ ንጉሡም እግዚአብሔር አምላኪየ ሆይ ምን ኃጢአቱ ቢበዛ ነው ከዚህ ምድረ በዳ ላይ ይህን ጽኑዕ ሕመም ያመጣሁብኝ ብሎ በትረ መንግሥቱን አንሥቶ ተመርኩዞ ቁሞ እያዘነና እየተከዘ ከጸለየ በኋላ በበትረ መንግሥቱ ከተመረኮዘበት ላይ ውሃ ፈለቀ በዚህ ጊዜ ንጉሡ በውኃው ተጠምቆ ዳነ ሠራዊቱም በጣም ተደነቁ እግዚአብሔርንም አመሰገኑ በንጉሡ በትረ መንግሥት የፈለቀውን ውሃም ንጉሡ በትካዜ ሲጸልይ ስለፈለቀ ትካዜ ወንዝ ብለው ሰየሙት ይባላል ። ደብስ የተባለውም ቦታ ንጉሡ ከሕመሙ ብዛት የተነሣ መልኩ ተለውጦ ደብዘዝ ጠቆር ስለአለ ደብስ ተብሏል ቀዳማዊ ምኒልክ በዚያ ቦታ ላይ ግብር አድርጐ አበላ አጠጣ በተአምራትም ከወደቱ እንደመጡ ሳይታወቁ አምሳ ጊደሮችና ፹ ተሮ ንብ መጥተው ከንጉሡ ድንኳን አጠገብ ሰፈሩ ንጉሡና ሠራዊቱ ተመልክተው እግዚአብሔርን አመ





www.ethiopianorthodox.org

ሰገኑ ንግሡም ይህ በቀር የመጣው የንብ ማር ተቆርጦ በክብር ለመድኃኒት በዕቃ ይቀመጥ ንቦቹ ግን ልምላሜ ወደአለበት ቦታ ይወሰዱ ገደሮቹ ደግሞ የተከዜን ምንጭ ለሚንከባከቡና ለሚጠብቁ ሰዎች ይሰጡ ብሎ ከተከዜ ምንጭ አጠገብ ዛሬ ፶ ገደር የሚባል ይገኛል ፶ው ቀፎ ንብ የተሰማራበትም መነር ገደል ይባላል ዛሬ እየላ ቅዱስ ሚካኤል ከሚባለው ቤተ መቅደስ ትንሽ ጉዞ እንደአደረገ ድንኳን በማስተከል ዕረፍት አደረገ ከዚያም ከአራት ቦታ ላይ አስደናቂ ውሃ ፈለቀ ቅዱስ ሚካኤልም በዚያ ቦታ ላይ በሰው አምሳል ተገልጾ ይህን ቦታ ከእግዚአብሔር ዘንድ እኔ የተረከብኩት ስለሆነ ዳሩ እሳት መሐሉ ገነት እንዲሆንልኝ ከልልልኝ ዳር ድንበሩ የተከበረ እንዲሆንልኝ ብሎ ለንጉሡ ነገረው ይባላል ፡ ንጉሡም ዳሩ እሳት መሐሉ ገነት ይሁንልህ ለእኔም ለሠራዊቱም የሚያስደስት ከ፬ ቦታ ላይ ውሃ ስላፈለቀልኝ ይህ ቦታ የውሃ ምንጭና የሀል በረከት አይጉደልበት ብሎ ንጉሡ መርቆ ሲነሣ ሊቀ ካህናቱ አዛርያስ የያዘው ታቦት አልንቀሳቀስም ብሎ እየለ ንጉሡም ይህን ታቦት ከታቦተ ጽዮን ጋር ኢየሩሳሌም ያመጣሁት በመናገሻ ከተማዬ ላይ ቤተ መቅደስ ሠርቼ ላስቀምጠው ነበር ። በተለይ የቅዱስ ሚካኤል ታቦት እኔ ሀገር ለመጐብኘት ስዘዋወር አብሮ ከእኔ ጋር ይዘምታል ብዬ ነበር ምን ይሻለኛል? ብሎ ከሊቀ ካህናቱ አዛርያ ጋር ሰባት ቀን ሲጸልዩ ሰንብተው ታቦቱን አንሥቶ ለመጓዝ ቢሞክር አሁንም የማይቻል ሆነባቸው ። ዳግመኛም ቅዱስ ሚካኤል በገሃድ ተገልጾ ንጉሥ ሆይ አስቀድሜ እንደነገርኩህ ይህ ቦታ ከእግዚአብሔር አምላኪዬ የተሰጠኝ ስለሆነ ይህ ታቦት ከአንተ ጋር መሔድ የለበትም በክብር ቦታ ሠውረህ አስቀምጠኸው ሒድ ብሎት ከፊቱ ተሠወረ ይባላል ።

በዚህ ጊዜ ንጉሡ ቀዳማዊ ምኒልክ የእግዚአብሔርን ረቂቅ ጥበብ ተመልክቶ አደነቀ ይህን በቅዱስ ሚካኤል ስም የተሰየመውንም ታቦት ከአጠገቡ በሚገኘው ጥድ ዛፍ ግንዱን አስፈልፍሎ በዚያ ውስጥ ለማስቀመጥ ቢያሥነሣው ሳያስቸግር ታቦቱ በሊቀ ካህናቱ አዛርያስ እጅ ተነሥቶ በዚያ በጥድ ዛፍ ግንድ በተፈለፈለው ስውር ቦታ ገብቶ እንዲቀመጥ ተደረገ ።

ከዚህ በኋላ ንጉሡ በዚህ ቦታ ላይ ደብተራ ኦሪት ምኩራብ አይሁድ ምኩራብ እስራኤል ይሠራበት ብሎ አሁ ታላቅ ቤተ መቅደስ አሠርቶበት ወደ መናገሻ ከተማው አክሱም ጽዮን ተመልሶአል ። ይህም ቦታ ጥንተ ስሙ መዘላ ይባል ነበር የቅዱስ ሚካኤል ታቦት አልነሣም ብሎ በማየሉ ምክንያት እየላ ቅዱስ ሚካኤል ተባለ ይባላል ።

በዚህም ታሪካዊ ቦታ ላይ የሥርዓተ ኦሪትን ሥነ ሥርዓት የሚፈጽሙ ካህናተ ኦሪት ንጉሡ ቀዳማዊ ምኒልክ ከሊቀ ካህናቱ ከአዛርያስ ጋር ተመካክሮ ፲፪ ካህናተ ኦሪት ልኮለት እስከ ዘመነ ሐዲስና ክርስትና ጥምቀት ቁርባን እስከሚተካ ድረስ በአክሱም ጽዮን ይፈጸም የነበረው ሥርዓት እየተፈጸመበት ኖሮአል ።

በ፫ኛው መቶ ዓመተ ምሕረት አጋማሽ ላይ አብርሃ ወአጽብሐ የተባሉት የክርስቲያን ነገሥታት ወደዚህ እየላ ቅዱስ ሚካኤል ወደተባለው መጥተው ለሰባት ቀናት ሱባኤ ካደረጉ በኋላ የቅዱስ ሚካኤልን ታቦት ከተሠወረበት በጳጳሱ በአቡነ ሰላማ እጅ አስወጥቶ አስባርኮ ሥርዓተ ኦሪት ይፈጸምበት በነበረው ቦታ ላይ ታላቅ ቤተ መቅደስ ተሠርቶ የመልአኩ ቅዱስ ሚካኤል ታቦት ገብቶ ቅዳሴ ቤቱ በ፫፻፴፬ ዓ ም ኅዳር ፲፪ ቀን መከበሩን በደብሩ የተጻፈ ታሪክ ይገልጻል ከዚያ ዘመን ጀምሮም ከ፲፪ ቦታ ላይ ልዩ ልዩ በሽታና ደዌ ለያዛቸው ሰዎች የሚፈውስ ጸበል ፈልቋል ይህ ጸበልም ከፈዋሽነቱ የተነሣ በዚህ ቦታ ከየአውራጃው እየመጡ የሚፈወሱት ምዕመናን ብዙ ናቸው ። ታቦቱም ፈጥኖ የሚሰማ ተአምረኛ ታቦት ነው በፈጥኖ ሰሚነቱም ዓፄ እንበሳ ውድም ቤተ መቅደሱን አድሶለታል ከዚያም ቅዱስ ሀርቤ ንጉሥ አድሶታል ከዚህ በኋላ ዓፄ ዘርአያዕቆብ በቦታው ተገኝተው በአማረ ሁኔታ በግንብ አሠርተው መቅደሱንና ቅድስቱን በልዩ ልዩ መንፈሳዊ ሥዕል አሥለውታል ቀጥሎም ዓፄ ገላውዴዎስ በቦታው ተገኝተው የዓፄ ዘርአያዕቆብን ሥራ አሻሽለው አድሰውለታል አድያም ሰገድ ኢያሱም በዚሁ እየላ ቅዱስ ሚካኤል ተገኝተው በጸበሉ ተጠምቀው የጸበሉን ቦታ የቤተ ክርስቲያኑን ቅጽር የጣራ ክዳኑን በሚገባ አድሰውና አሠርተው ለቤተ ክርስቲያኑ ብዙ ርስትና ጉልት ብዙ ካህናት ተክለውለት ተመልሰዋል ከዚህ ሌላ ዓጼ ዮሐንስ የተከዜን ምንጭ ለመጐብኘት መጥተው እየላ ቅ.ሚካኤልንም ጐብኝተውታል ።

በመጨረሻም ዳግማዊ ዓጼ ምኒልክ የአባታቸውን የቀዳማዊ ምኒልክን ትክልና የተከዜ ወንዝ ምንጩ እንዴት እንደፈለቀ ለማየት ሔደው ከተመለከቱ በኋላ የእየላ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ መቅደስ ሥዕሉን በሚገባ አሳድሰው ከተከዜ ምንጭ እስከ ሻልና ሳንቃ ከሚገኘው ሀገር የአሥራት ገቢ ከ፲ አንድ ሰጥተው ደብሩን በሚገባ አድሰው ከየጁ ውስጥ ፶ ገባር መሬት ሰጥተውታል ። ብዙም የወርቅና የብር መስቀል ጽዋዕ አልባሳት ሰጥተውታል ይህ ታሪካዊ ደብር በዚህ ሁኔታ እንደተከበረ እስከዛሬ ድረስ መንፈሳዊ አገልግሎት ሲፈጸምበት ይገኛል የጸዋትወ ዜማ የመጻሕፍት ትርጓሜ መምህራንም እስከአሁን ድረስ በማስተማር ይገኙበታል ቦታው ወይና ደጋ ስለሆነ አጃ ፡ ስንዴ ፡ ገብስ ፡ ባቄላ ይመረትበታል የተክል ዓይነት ሎሚ ፡ ትርንጐ ፡ ጌሾ፡ ኮሶ ፡ ጥድ አንዳንድ አርቲሻልና ቁጠማ ይበቅልበታል የክረምቱ ወራት በዓመት ሁለት ጊዜ ስለሆነ በየመቱ ሁለት ጊዜ አዝመራ ይዘመርበታል ይዘራበታል የማያቋርጥ ውሃ በብዛት ስለሚገኝ የመስኖ አዝመራ ይመረትበታል ። ጠቅላላ የበልግና የክረምት አዝመራ የመስኖ አዝመራ የሚገኝበት እርጥብና ልምላሜ የማይለየው ለከብቶች ግጦሽ ማር እንደልብ የሚገኝበት ቦታ ነው ። ከዓመት እስከ ዓመት ቅዳሴ ይቀደስበታል ጸሎተ ዕጣን ይደረስበታል በዓበይት በዓላትና በጾመ እግዚእ ጾመ ድጓ ሰዓታት ይደረስበታል ብዙ የብራና መጻሕፍትና የወርቅ የብር መስቀልና አልባሳት ጥንታዊ የሆኑ ዕቃዎች ይገኙበታል ።

ይህን ታሪካዊ ቦታም ለሚጐበኙ በአጠገቡ ወደ ቅዱስ ላሊበላ ደብር የሚሔድ መኪና ስላለ በመንገድ በኩል ችግር የለም በዚህም ምክንያት ብዙ የውጭ ሀገር ቱሪዝምና ጋዜጠኞች ከእየላ ቅዱስ ሚካኤል አጠገብ የተከዜ ወንዝ የመነጨበትን ቦታ ለማየት ሲሔዱ እግር መንገዳቸውንም የእየላ ቅዱስ ሚካኤልን ቤተ ክርስቲያን ሳይጐበኙት አያልፉም የቤተ ክርስቲያኑ የውስጥ የግድግዳ ጥንታዊ ሥዕልም አስደሳች ስለሆነ በፎቶግራፍም እያነሡ የሚያመጡት የውጭ ሀገርና የሀገር ውስጥ ጐብኚዎች እጅግ ብዙዎች ናቸው ።

እንግዲህ የእየላ ቅዱስ ሚካኤል ቤተ ክርስቲያን የተከዜ ምንጭ መፍለቂያ ጉረቤትና አዋሳኝ ከመሆኑም በላይ በቤተ ክርስቲያኑ አጠገብ እንደተከዜ ምንጭ ወበተከዜ የኀልፉ በእግር ታላላቅ ነገሥታት በእግራቸው ያልፉበታል ብሎ ነቢዩ ዳዊት የተነበየለት ይህ ወንዝ ነው ሊባል ይቻላል ከእየላ ቅዱስ ሚካኤል እስከ ተከዜ ወንዝ ምንጭ የሚያስኪደው የእግር ጉዞ ከ፲፰ ደቂቃ እስከ ፴ ደቂቃ ነው ።

የቀንድ ከብትና የጋማ ከብት በብዛት የሚገኙበት ከመሆኑም በላይ ልዩ ልዩ የዱር አራዊቶችም ይገኙበታል ከላስታ አውራጃ ቀደምትነትን ይዞ የሚገኘውም ይህ እየላ ቅዱስ ሚካኤል ነው ይህን ታሪካዊ ቦታ ለመጐብኘት ሁላችንም እንሽቀዳደም ።

ይህ ከዚህ በላይ የሚገኘውን ዝርዝር ታሪክ ይዞ የሚገኘውም የዚና ወረሲዎችን ታሪክ የሚናገረው መዝክረ ወረሺህ የሚባለው መጽሐፍ ነው ይህ መጽሐፍም የሚገኘው በገነተ ልዑል ማርያምና በተድባበ ማርያም ደብር ዕቃ ቤት ነው እንግዲህ ከዚህ በላይ ከጥንት አባቶቻችን ሲያያዝ መጥቶ ሲተረክ የነበረውን ታሪክ አቅርበንላችኋልና ሁላችሁም የምርምር ሰዎች እንድትሆኑ ተጋብዛችኋል ።


የታሪኩ አቅራቢ
አባ ገብረ መስቀል ተስፋዬ
ዘገነተ ማርያም


# ዕለተ ምሳሌ

(ምሳሌነት ያላት ዕለተ ሰንበት)


ከመ አ ኢ መክብብ አጥናው


ቁጥር ፩፡—

እግዚአብሔር ሰባተኛውን ቀን ባረከው ቀደሰውም ።

እዚህ ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ዕለተ ቀዳሚት ሰንበት ናት ። ይህችም ዕለት መድኅን ዓለም ክርስቶስ በለበሰው ሥጋ የሞትን ጽዋ ከተቀበለ በኋላ ከሙታን ተለይቶ ለተነሣባትና "የጌታ ቀን" እየተባለች የምትጠራው የእሁድ ሰንበት ምሳሌ ናት ። ይህችም ቀዳሚት ሰንበትን የምትተካ የእሁድ ሰንበት እንደገና ጌታ ይህን ዓለም ለማሳለፍ በሚመጣበት ጊዜ የመጨረሻ ፍርድ የሚሰጥባት ዕለት ስለሆነች ሊቁ አትናቴዎስ "እግዚአብሔር ድንቅ ሥራውን የገለጠባት የዕለታትና የበዓላት ሁሉ በኩር ናት በማለት በቅዳሴው ያወድሳታል ።(፩)

ቁጥር ፪፡

አንድ አይነት ጉም ከምድር ወጥታ እየተሳበች መሬትን ታጠጣ ነበር ።

ገና ዝናም ከመጀመሩ በፊት ለእዝርዕት ለአትክልትና ዛፎች ሁሉ ሕይወትን የምትሰጥ የጠል መገኛ የሆነች ያች ጉም የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ ነበረች ። ለምዕመናን ሕይወት ጠለ ምሕረትና የመንፈስ ተሐድሶ የሚገኝ ከርሱ ነውና ።

ቁጥር ፫፡

እግዚአብሔር ከመሬት አፈር ነሥቶ የፈጠረውን ሰው በአፍንጫው እፍ ብሎ የሕይወትን እስትንፋስ አሳደረበት ሰውም ሕይወት ያለው ፍጥረት ሆነ ።

የሰው ተፈጥሮው ከሌሎች ማለትም በደመ ነፍስ ሕያዋን ሆነው ከሚኖሩት ፍጥረታት ሁሉ የሚለየው በሦስት ዋና ዋና ነገሮች ነው ይኸውም ፡

ሀ. በሰው ሕይወት ውስጥ ለዘለ ዓለም የማትሞት ሕያዊት፡ ለባዊት (ማስተዋል የምትችል ና) መንፈሳዊ አካል ያላት




www.ethiopianorthodox.org

ነፍስ አለችው ። ይህንንም ሰሎሞን በመጽሐፈ መክብብ ሲገልጽ "መንፈስ ወይም የሰው ነፍስ ሥጋ በምትለይበት ጊዜ ወደሰጭዋ (አስገኝዋ ወደ ሆነው ወደ እግዚአብሔር ትመለሳለች) ። ብሏል (መክ.፲፪፡፯)።

፪. የማሰብ ኃይሉ በደመ ነፍስ ሕያዋን ሆነው ከሚኖሩት ፍጥረታት ሁሉ የላቀ መሆኑና

፫. በተፈጥሮው የእግዚአብሔር አርአያ መልክዕ የተማለበት ሆኖ መገኘቱ ልዩ መታወቂያው ሆኗል ።

"በአፍንጫው እፍ ብሎ የሕይወት እስትንፋስ አሳደረበት" በሚለውም አንጻር ከዚህ አባባል ጋር በተገናዘበ ሁኔታ ክርስቶስ በደቀ መዛሙርቱ ላይ እፍ ብሎ የመንፈስ ቅዱስን ጸጋ እንዲያድርባቸው አደረገ (ዮሐ .፳፡፳፪)ይላል ። ይህም የነፍስን ተሃድሶ የሚያመለክት ነው።

በሌላ ትርጉም የመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ራሱ እግዚአብሔር እስትንፋስ ተብሎ ይጠራል ። ለዚህም ማስረጃ "ይህ እኔ የምነግራችሁ ቃል መንፈስ ነው ሕይወትም ነው" ። ሲል ክርስቶስ ራሱ የተናገረው ቃል በቂ ምስክር ነው ። (ዮሐ ፮፡፷፫) ።

## የሕይወት ዛፍ

በቁጥር ፱፡

በዔደን ገነት ከነበሩት ተክሎች መካከል የሕይወት ዛፍ ተብሎ የሚጠራ ተክል እንደነበር ይገለጣል ። የዚያም ዛፍ ፍሬ ሺህ ዓመት ታድሶ ለመኖር የሚያስችል እንደነበር በዘፍ .፫፡፳፩ የተጻፈው ቃል ያስረዳል ።

ታዲያ ያ ዛፍ የዘለዓለም ሕይወትን ለመስጠት በማዕከለ ዘመን በተዋህዶ ሥጋ የመጣ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር ። ይህንም ምሥጢራዊ ምሳሌ በትርጉም ያገናዘበው ሊቅ ቅዱስ ኤፍሬም "ከፈለነ ንብላእ እምዕፀ ሕይወት ዘውእቱ ሥጋሁ ለክርስቶስ ወደሙ ክቡር እግዚአብሔር ዳግመኛ ከዚያ ከሕይወት ዛፍ ፍሬ እንድንበላ ፈቀደልን ። እርሱም የክርስቶስ ሥጋና የክቡር ደሙ ምሳሌ ነበር ።" ሲል ገልጦታል ።(፩)

## የአራቱ ወንዞች ታሪካዊ ምሳሌነት

በቁጥር ፲ ፲፭ ከገነት የሚፈልቅ አንድ ትልቅ የፈሳሽ ውሃ ወንዝ ከአራት ተከፍሎ አራቱን ማዕዘነ ዓለም እንደሚያጠጣ ይናገራል ።

— ያም ወንዝ የክርስቶስ ምሳሌ ነበር ፡

— አራቱ ወንዞች ኤፌሶን ፡ ግዮን፡ ጤግሮስና ኤፍራጥስ ተብለው ይጠራሉ ። እነርሱም አራቱ ወንጌላውያን ተብለው የሚጠሩት የማቴዎስ ፡ የማርቆስ ፡ የሉቃስና የዮሐንስ ምሳሌዎች ነበሩ ።

ውሃው በአንድ በኩል የእግዚአብሔር ቃል ምሳሌ እንደነበር በመዝ.፩—፫ ፡ ሕዝ .፵፯፡፩—፲፪ የተጻፈው ምሳሌ ያስረዳል ።

— በሌላ በኩል ውሃ የመንፈስ ቅዱስ ምሳሌ መሆኑን ክርስቶስ ተናግረዋል (ዮሐ.፯፡፴፰) ።

— አራቱ ወንዞች በአራቱ ማዕዘነ ዓለም ተሠራጭተው ለፍጥረት ሁሉ ሕይወትና ልምላሜን እንደሚሰጡ አራት ክፍል ሆኖ በአራቱ ጽሕፈት የተጻፈውም የወንጌል ቃል በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ለመላው ዓለም ጽንፍ እስከ ጽንፍ መድረሱን ያመለክታል ።

— ሁኔታው ልክ እንደ አራቱ አፍላጋት ስርጭት መሆኑን ከሊቃ አትናቴዎስ ድርሳን መረዳት ይቻላል እርሱም፡— ቦ ዘይነቅዕ እምሥራቅ ወየሐውር ለምዕራብ ከመይስቂ ቦህየ ። ከምሥራቅ መንጭቶ ወደ ምዕራብ ከምዕራብ ወደ ምሥራቅ ፡ ከሰሜን ወደ ደቡብ በመተላለፍ በዚያ ያለውን ያጠጣ ዘንድ የሚፈስ አለ የሚል ነበር ። የትምህርተ ወንጌልም (የቃሉ) ሥርጭት ልክ እንደ ዚሁ ነው ።

ዛሬስ ይህ ቃለ ሕይወት ለብዙዎች ነፍሳት እንዲደርስ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ ተልዕኮ የቀድሞይቱን ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ ሕይወት የተከተለ ነውን?

"የእግዚአብሔር ቃል ለሁሉ እንዲዳረስ ጸልዩልን (፪ኛ ተሰ.፫፡፩—፫)። የሚሉ ወንጌላውያን በብዛት አሉን?

አልቦ ነገር ወአልቦ ነቢብ ዘኢተሰምአ እምቃሎሙ፡— ድምጻቸው በዓለም ሁሉ ተሰማ ፡ ቃላቸውም እስከ ምድር ዳርቻ ደረሰ" ተብሎ የተጻፈው ትንቢት ተፈጽሟል ማንም ሰው ቃሉን አልሰማሁም ማለትስ ይችላልን? ሰው ሆይ "እነሆ" ቃሉ ለአንተ ቅርብ ነው በአንደበትህና በልብህ ጽላት ተጽፎ ስለሚገኝ ልትፈጽመው ይገባል ። (ዘዳግ.፴፡፲፬)

ቁጥር ፲፭፡—

እግዚአብሔር አምላክም ሰውን ወስዶ ያበጃትና ይጠብቃት ዘንድ በዔደን ገነት አኖረው ።

— የሥራ ክቡርነት ከዚህ ጀምሮ ይታያል ። በዘፍጥረት ፫፡፲፱ የተጻፈውን ቃል በጥራዝነጠቅነት አመለካከት በመጥቀስ ሥራ በዕርግማን የመጣ የሚመስላቸው ሁሉ በቅድሚያ ከጥንት ጀምሮ የነበረውን የሥራ ክቡርነት በማስተዋል በሀዲስ ኪዳን ትምህርት "ለመሥራት የማይወድ ቢኖር አይብላ" ተብሎ የተጻፈውን መሪ ቃል ማስታወስ ይገባቸዋል ።

የህም ለወንጌል ሥራ ምሳሌ ሆኖ ሊጠቀስ ይችላል ።

ለማስረጃም ያህል፡—

— አዝርዕትና አትክልት አራሚና ኮትኳች እንደሚያስፈልጋቸው የአማኞች (የምዕመናን) ሕይወት የበጎ ሥነ ምግባር ፍሬ መገኛ ይሆን ዘንድ በቃለ እግዚዘአብሔር ፡ በምክርና ተግሳጽ አርመው ኮትኩተው ገርዘው የሚያስተካክሉ መምህራን ካህናት ያስፈልጋሉ ።

— አዝርእትና አትክልት ከተባይ የሚጠበቁበት አጥር ቅጥር እንደሚያስፈልጋቸው ምዕመናንም ከክህደትና ከክንቱ ጥርጣሬ ተጠብቀው የሚኖሩበት ሕገ እግዚአብሔር ስለሆኔ ወንጌል በምልእት መሰበክ አለበት ።

— የአንዳንድ አዝርዕትና አትክልት ወይም የዛፎች እድሜ በአጭርና በረጅም ጊዜ የተወሰነ ነው ። የሰውም እድሜው ከዚህ ጋር ተመሳሳይ መሆኑን መዝሙረኛው ነቢዩ ዳዊት ሲገልጽ "ተዘከር እግዚኦ ከመ መሬት ንሕነ ወስብእስ ከመ ሣዕር መዋዕሊሁ፡— እኛ አፈር ትቢያ መሆናችንን አስብ ፡ የሰው ሕይወት ዛሬ ታይቶ ነገ እንደሚረግፍ ሣርና እንደ ጽጌረዳ አበባ ነው ።" ብሏል ። በነቢዩ ኢሳያስም ትንቢት "የሕዝቤ ዕድሜ እንደ ዛፍ ዕድሜ ይሆናል ፡ እኔም የመረጥኋቸው በእጃቸው ሥራ ረጅም ዘመን ደስ ብሏቸው ይኖራሉ፡ እነርሱ ከነልጆቻቸው የእግዚአብሔር ብሩካን ልጆች ናቸውና በከንቱ አይደክሙም" ተብሎ ተጽፎአል ። (ኢሳ.፷፭፡፳፪—፳፫) ።

ታዲያ ገና በጥንተ ፍጥረት የገነትን ተክሎች በመኮትኮት በመግረዝና በመንከባከብ የምድሪቱን አፈር በመጠበቅ እንዲሠራ ቀዳማዊ አዳምን ያዘዘው ጌታ እግዚአብሔር ዛሬም የሐዲስ ኪዳን ተክል የሆኑ ምዕመናንን የሚጠብቁ ቃሉን የሚመግቡና የሚንከባከቡለትን የወንጌል አዝመራ (መከር) ሰብሳቢዎችን ሠራተኞችን በብዛት ይፈልጋል ። (ማቴ.፱፡፴፯—፴፰ ፡ ፳፡፩—፲፯ ፡ ሉቃ. ፲፫፡፮—፱) ።

## ምሳሌነት ያለው የመጀመሪያ ሕግ

ቁጥር ፲፯፡—

እግዚአብሔር አምላክ የፈጠረውን ሰው "ክፉና በጎውን ለይቶ ለማወቅ ከሚያስችል ከዚያ ዛፍ ፍሬ እንዳትበላ ተጠንቀቅ ከርሱ በበላህ ቀን ሞትን ትሞታለህ" ብሎ አዘዘው ።

ገና ከመጀመሪያ የሰው ዘር አኗኗር ሥርዓት አንሥቶ ሲታይ ከአንድ ዓይነት ምግብ መካከል ወይም መጾም በእግዚአብሔርና በሰው መካከል የአዛዥነትና የታዛዥነት መታወቂያና ተቀዳሚ ሕግ ሆኖ ብቅ ማለቱን ከዚህ ጥቅስ እንገነዘባለን ።

## የአብርሃ ወአጽብሐ ታሪክ በአጭሩ

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከጥንት ጀምራ ከአምልኮተ ጣዖት ርቃ ፈጣሪዋን አውቃ በታሪክ ተደንቃ የኖረች ናት ፡ ቅድስት ቤተ ክርስቲያናችን ከልደተ ክርስቶስ በፊት ለብዙ ዘመናት እምነተ ኦሪትን ስትከተል ከቆየች በኋላ ፡ በመጀመሪያ የክርስትና እምነት አጀማመርና አነሣሥ በአንደኝነት ደረጃ የታወቀች እንደሆነች የንግሥት ህንደኬ የገንዘብ ሚኒስቴር ከነበረው ጃንደረባ ታሪክ እንረዳለን ።

ከዚህ በኋላም ቢሆን ሐዋርያው ቅዱስ ማቴዎስ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስነት ክርስትናን እንደአስተማረ ብዙ የታሪክ መረጃዎች አሉን ፡ የኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያን መንበረ ማርቆስ ሥር ናት ብለው ያምኑ የነበሩት የእስክንድርያ ሊቃውንት ስንኳ ይህን የታሪክ እውነታ መሸፈን ስላልተቻላቸው በየታሪክ ዓምዶቻቸው አስፍረውታል ።

ቢሆንም ግን በ፬ኛው ክፍለ ዘመን ማለት ከ፫፻፳፰ እስከ ፫፻፴፪ ባለው ጊዜ ውስጥ በራስዋ ልጆች ሐዋርያነት እምነተ ክርስትናን ፡ በተስተካከለ ሁኔታ ተቀብላለች ። እነዚህም ሐዋርያት ልጆችዋ አብርሃ ወአጽብሃ ከአባታቸው ከአክሱማዊው ንጉሥ ታዜር ስመ መንግሥቱ ሰይፈ አርዕድ ነገድዋ ከሌዋውያን ትውልዱ በትግራይ ክፍለ ሀገር ከዓይበገማድ ከሆነችው ከእናታቸው ንግሥት ሶፍያ በስእለት ተወለዱ ።

ንጉሥ ታዜርና ንግሥት ሶፍያ ልጅ ባለመውለዳቸው ሲያዝኑና ሲተክዙ ከቆዩ በኋላ አንድ ጊዜ ቅድስት ሶፊያ ቤተ እግዚአብሔር ገብታ ንጉሥ ታዜር ከቤተ መንግሥቱ ሆኖ ሁለቱም ሱባኤ በመግባት ንጽሐ ልቦና ባለው እንብእ ልጅ እንዲሰጣቸው እግዚአብሔርን ለመኑ እግዚአብሔርም ልመናቸውን ሰምቶ ልጅ እንዲሰጣቸው በመልአኩ በቅዱስ ሚካኤል ቃል በራዕይ አበሰራቸው ። (ነገራቸው) ።

ንጉሡና ንግሥቲቱ እግዚአብሔር በመልአኩ የነገራቸውን ቃል ተቀብለው ልጅ እንደሚወልዱ ያለመጠራጠር በፍጹም እምነት ደስ





www.ethiopianorthodox.org

ብሎአቸው እግዚአብሔርን አመሰገኑ ። ንግሥት ሶፍያም መጋቢት ፳፱ ቀን ፲፶ ዓመተ ምህረት ገደማ ጸነሰች።

ሶፊያ እንደ ጸነሰች በሁሉም ዘንድ ተሰማ ሁሉም በያለበት ለእግዚአብሔር የሚሳነው የለም እያለ እግዚአብሔርን አመሰገነ ።

ሶፍያም የጽንሷ ወራት ከተፈጸመ በኋላ ታህሳስ ፳፱ ቀን ፲፶፩ ዓ.ም. ፀጋ እግዚአብሔር ያደረባቸው ፊታቸው እንደ ፀሐይ የሚያበራ ሁለት ልጆችን (መንትያዎችን) ወለደች የልጆቹም ስም አዝጓ ተባለ ።

እንደዚህ መባላቸው አባት እናታቸው በሰዎች ዘንድ ፀሐይን በረከት እየተባሉ ይሰደቡ (ይታሙ) ስለነበር እግዚአብሔር ስድብን ከኛ አርቀዋል ሲሉ ነው ።

በስዕለት የተወለዱ አብርሃ ወአጽብሐ መጻሕፍተ ሃይማኖትንና ሌሎች ጥበባትን ከሊቀ ካህናቱ ከአንበረም እየተማሩ በቤተ መቅደስ ውስጥ ፯ ዓመት ሲሆናቸው በፈሪሃ እግዚአብሔርና በጥበበ እግዚአብሔር ታንፀው አደጉ ከተወለዱ ፲፪ ዓመት ሲሆናቸው አባታቸው ንጉሥ ታዜር ስለሞተ በእግዚአብሔር ፈቃድ ሁለቱም የአባታቸውን መንበረ መንግሥት ተረከቡ ፤ ስማቸውም ዒዛና ሳይዛና ተባለ ።

ሁለቱም እንደ አንድ ልብ መክረ እንደ አንድ ቃል ተናጋሪ በመሆን በመንፈሳዊ ጥበብ እየተራቀቁ የእግዚአብሔርን ሕልውና ለሰው እያሳወቁ የማይመረመር ረቂቅ ጥበቡን እያደነቁ ለ፲፫ ዓመታት ኢትዮጵያን ካስተዳደሩ በኋላ በመንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ሥርዓት ጥምቀትን እንዲያመጣላቸው ፍሬ ምናጦስን (አቡነ ሰላማን) ወደ እስክንድርያ ወደ ቅዱስ አትናቴዎስ ላኩት ቅዱስ አትናቴዎስም በሁኔታው ተደስቶ እግዚአብሔርን በማመስገን ፍሬ ምናጦስን ጳጳስ ሹም ሲልከው ሰላማ ብሎ ሰየመው ።

ብፁዕ አቡነ ሰላማ ከቅዱስ አትናቴዎስ የተቀበሉትን ጠቅላላ ሥርዓት ይዘው ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ በመጀመሪያም ሁለቱ ወንድማማቾች ማለት ዒዛና እና ሳይዛና ተጠምቀው አብርሃ ወአጽብሐ ተባሉ ፤ አብረሃ ወአጽብሐ ሲጠመቁ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ፍቅሩን ይገልጽላቸው ዘንድ ከቅድስት እመቤታችን ጋር መላእክትን አስከትሎ በጥምቀታቸው ጊዜ እንደተገኘ ገድላቸው ያስረዳል ። አብርሃ ወአጽብሐ ከተጠመቁ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ገልጾላቸው እንደ ሐዋርያት ብዙ ቋንቋዎችን ተናግረዋል ።

እንዲሁም ሕሙማንን እንዲፈውሱ ሙታንን እንዲያስነሱና አጋንንት እያወጡ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ወንጌልን እንዲያስተምሩ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ሥልጣን ሰጥቷቸዋል ።

ቅዱሳን አብርሃ ወአጽብሐ ከአምላካቸው በተሰጣቸው ስልጣን ከአባ ሰላማ ጋር የማስተማርና የማጥመቅ ሥራቸውን ቀጠሉ ። በኢትዮጵያ ቤተ ክርስቲያንም ወንጌል ተሰበከች ሃይማኖት ጸናች ።

አብርሃ ወአጽብሐ ጥምቀተ ክርስትናን እና ሥርዓተ ክርስትናን ከማስፋፋት ጋር ለመጀመሪያ በአክሱም ፲፪ መቅደስ ያለው በአምስት አምስት ክፍል የተከፈለ ባለ ፸፪ አእማድ (ምሶሶዎች) ቤተ ክርስቲያን በእመቤታችን በቅድስት ድንግል ስም ሠሩ። የቤተ ክርስቲያኑ ሥራ በዓለም ውስጥ መሰል ያልተገኘለት ዕፁብ ድንቅ የሚያሰኝ ነበር ።

አብርሃ ወአጽብሐ ኃይለ እግዚአብሔር ሳይለያቸው አጋንንትን ድል እየነሱ ልዩ ልዩ ተአምራትን እያሳዩ ሐዋሪያዊ ተግባራቸውን ሳያቋርጡ ወንጌልን ያስፋፉ ነበር ።

የእናታቸው የቅድስት ሶፍያ አገር በሆነችው በዓባይ ገማድ ሲያስተምሩ ከባድ ፈተና ገጥሟቸው እንደነበር ታሪካቸው ያስረዳል ። ይኸውም አጋንንት በሰው እያደሩ የሰውን አስተሳሰብ በመበከል እምነታችንና ልምዳችንን አንለውጥም እያሉ ከእምነት ጣዖት ቀላቅለው ይዘውት የነበረውን እምነት ስለ ነበር በሰው ኅሊና አድረው ሲያስቱ የነበሩትን መናፍስት ርኩሳንን እንደሰው ድንጋይ እያሸከሙ ያባርሩዋቸው ነበር ፤ ከዚህም ሌላ ብዙ ተአምራትን አሳይተዋል ።

እንዲህ የመሰለ ተዓምራት ለመስራት ታላቅ ፀጋ የተሰጣቸው አብርሃ ወአጽብሐ በሥራቸው ሁሉ ከውዳሴ ከንቱ ከትዕቢትና ከተንኮል የራቁ ነበሩ ።

የአክሱምን አስደናቂ ቤተ ክርስቲያን ሠርተው ከፈጸሙ በኋላ ዛሬ ቅዱስ አጽማቸው በሚገኝበት ገዳም ቤተ ክርስቲያን እንዲሰሩ በፈቃደ እግዚአብሔር ተነሱ ቤተ ክርስቲያኑን የሚሠሩበት አመች ቦታ በመፈለግ ላይ እንዳሉ ውሃ ጠምቷቸው ወደ እግዚአብሔር ቢያመለክቱ ወተትና ማር አፈለቀላቸው ንሕነስ ኢለመድን ዘንተ ሲሳየ ብለው ቢጸልዩ ወተቱና ማሩ ወዲያውኑ ውሃ ሆነላቸው ያን ጊዜ ደስ ብሎአቸው ረከብነ ማየ ስላሉ ቦታው እስከ አሁን ድረስ ማየረከብነ (ማይረኽብና) እየተባለ ይጠራል ፤ ቅዱስ ሚካኤልም ቤተ ክርስቲያኑን ከዓለት ፈልፍለው የሚያሰሩበት እብነ አድማስ ሰጣቸው ።

፵፪ አእማድ ያሉበት በስፋቱ የታወቀ በሐረጉና በቅርጹ የተደነቀ በእርግጥም በሰው ተሠራ ብሎ ለመናገር የሚያስገርም ቤተ ክርስቲያን በእግዚአብሔር ኃይል እየተረዱ ሰሩ ፤



ይሕን ድንቅ ሕንጻ በሚሠሩበት ጊዜም ደመና እየጠቀሱ ጥዋት ጥዋት ከመንበረ መንግሥታቸው በመገኘት ፍትህ ርትዕ ያሚሉ ነበር ።

አብረሃ ወአጽብሐ ስለሠሩዋቸው አብያተ ክርስቲያናት ካነሳን ዘንዳ ታላላቅ አብያተ ክርስቲያናት ሌላ በጣና ሐይቅ በእመቤታችን ሥም ታቦተ ቂርቆስን ፤ በገርዓልታ ደብረ ማርያምን ፤ በመንዳዐ የቅዱስ ሚካኤልን ፤ በዓድዋ ውቅሮ ማርያምን ፤ በሐረማት ሕውዜንን ፤ በዓይባ ጉልብሻ ማረያምን ፤ በውቅሮ ቅዱስ ቂርቆስን ፤ በመደቂ ደብረ አብ ሥላሴን ፤ በአጽቢ ደብረ ስላምን ፤ በወሎ ተድባባ ማርያምን ፤ ጠለቃ በተባለች አገር ቁጥራቸው ያልተጠቀሱ አብያተ ክርስቲያናትን ሠርተዋል ።

አብርሃ ወአጽብሐ በእጃቸው የሠሩዋቸው አብያተ ክርስቲያናት ፰ መሆናቸውን በታሪክ የተመዘገበ ቢሆንም በትግራይ ፤ በሐማሴን ፤ በጎንደር ፤ በጎጃም ፤ በሸዋና በሌሎች ክፍላተ ሀገር አያሌ አብያተ ክርስቲያናትን በጊዜአቸው መታነጻቸውን ገድላቸው በሰፊው ያስረዳል ። ይህ ብቻ ሳይሆን በአክሱም ሐውልት ማቆማቸውንም በገድላቸው ተጽፏል።

አብርሃ ወአጽብሐ የትግራይንና የሐማሴንን ምዕመናን አስተምረው ካጠመቁ በኋላ በተከዜ በኩል ተሻግረው የጎንደርን ምዕመን አጠመቁ ፤ ከዚህ ደሴተ ጻና ሲደርሱ የደሴተ ጻና ሰዎች በምክረ አጋንንት ተሳስተው ባህላችንን አንጥለውም ወደ ደሴት የምትገቡትም ጀልባ አናቀርብም ስለአሉዋቸው ወደ እግዚአብሔር ሲጸልዩ ባህሩን በተአምራት አድርቆ አሻግሮአቸዋል ።

ከደሴቱ ገብተው ማስተማር ሲጀምሩ ምዕመናኑ ትምህርታቸውን ሰምተው ተአምራቸውን አይተው በመደነቅ ካመኑ በኋላ ብዙ ምዕመናን ተጠምቀዋል ከዚያም በጎጃም በየአውራጃዎቹ የነበሩትን አምልኮ ጣኦታት ፈጽመው አጥፍተዋቸዋል። አብርሃ ወአጽብሐ ሐዋሪያዊ ተግባራቸውን በመቀጠል ወደ ሸዋ ተጓዙ በዚያም ምድረ ኢረር ቤተ መንግሥት ሠሩ በዚያም በሌላው ክፍለ ሀገር እንደሚያደርጉት ሁሉ አጋንንትን እያወጡ ሕሙማንን እየፈወሱ የሸዋን አውራጃዎች ዞረው አስተማሩ በዚህ ሁኔታ እናሪያ ከዚያም ጅማና ወደ ልዩ ልዩ ቋንቋ ተናጋሪ ክፍሎች እየተዘዋወሩ ማስተማራቸውን ቀጠሉ በዚያ ጊዜም ምእመናን በዙ ፤ አብያተ ክርስቲያናት በብዛት ታነጹ ።

አብርሃ ወአጽብሐ ፲፫ ዓመታት ሙሉ ዞረው ካስተማሩ በኋላ አንዳቸው በትግራይ አንዳቸው በሸዋ ሆነው ሲያስተምሩና ሲያስተዳድሩ ወንጌል በበለጠ እንደምትስፋፋ ስለ ተማመኑበት አብርሃ በአክሱም አጽብሐ በሸዋ በመሆን ሐዋርያዊ ተልእኮአቸውን ፈጽመዋል

አብርሃ ከወንድሙ ከአጽብሐ ተለይቶ ለ፲ ዓመታት ያህል ከኖረ በኋላ በተወለደ በ፶፪ ዓመቱ ነፍሱን ለእግዚአብሔር ሰጠ ።

የአብርሃ አስከሬን አክሱም እንዲቀበር ፤ ሲጓዝ ቆይቶ በገርዓልታ ወረዳ መንዳዕ ከተባለች ቦታ ሲደርስ አስከሬኑን የያዘ ቃሬዛ እንደእሳት ግሎ አልነሳ አላቸው ፤ በዚህ ሁኔታ ሰዎች ተቸግረው እያዘኑ ሳለ እግዚአብሔር መልአኩ ቅዱስ ሚካኤልን ላበላቸው መልአኩም በአምሳለ አፍ ዐኋዳ ይለዋል በነጭ ወፍ አምሳል እየመራ በመንፈስ ቅዱስ ኃይል ወደ ሠሩዋት ቤተ ክርስቲያን ወሰዳቸው። ከዚህ በኋላ አባ ሰላማም ሆኑ ጃንዞመር የቅዱስ አብርሃ አስከሬን ማረፍ ያለበት መልአኩ ካሳያቸው ቦታ መሆኑን ተረድተው እግዚአብሔር ወደ ፈቀደው ቦታ ለመውሰድ አስከሬኑን ቢያነሱት ያለምንም ችግር ተነሳላቸው ።

ምዕመናኑም በተደረገው ተዐምራት በጣም ደስ ብሎአቸው እግዚአብሔርን እያመሰገኑ ነሐሴ ፲፫ ቀን በእለተ ደብረ ታቦር ምስካቡ ወደ ሆነችው ወደ ገዳመ አብርሃ ወአጽብሐ አገቡት ፤ ያን ጊዜ ወዲያውኑ የቤተ መቅደሱ ዙርያና አእማድ በጠቅላላ ውሃ ወተትና ማር አፍልቀዋል።

ይኸውም እስከ ዛሬ ድረስ በየዓመቱ ነሐሴ ፲፪ ቀን ጀምሮ ነሐሴ ፲፫ ቀን ከቅዳሴ በኋላ የሚደርቅ ፤ ጥቅምት ፫ ቀን ጀምሮ ጥቅምት ፬ ቀን ከቅዳሴ በኋላ የሚደርቅ ሲሆን በልዩ ልዩ ደዌያት የሚሰቃዩ ሕሙማን ይድኑበታል ።

አብረሃ ከሞተ በኋላ ወንድሙ አጽብሐ ምዕመናንን ፤ እያጽናና አብያተ ክርስቲያናትን እያስፋፋ ወንጌልን እያጠናከረ ለ፲፫ ዓመታት በቆየበት ጊዜ ሚስት አግብቶ ዘር እንዲተካ የእግዚአብሔር ፈቃዱ መሆኑን በቅዱስ ሚካኤል ቃል ስለተነገረው እንዲት ድንግል አግብቶ ልጅ ወለደ ። ልጁም አስፋህ ነው ፤ አጽብሐ አስፋህን ከወለደ ከ፲፪ ዓመታት በኋላ እንደ ወንድሙ እንደ አብርሃ በሰማዕትነት ጥቅምት ፬ ቀን አረፈ አስከሬኑ ከወንድሙ ከአብርሃ ጋር ተቀመጠ አጽብሐ በሕይወት የኖረበት ጊዜ ፷፰ ዓመት ሲሆን ከሱ በኋላም ልጁ አስፋህ ነግሠዋል ።

ቀ.ኃይለ ሥላሴ ዓለማየሁ
የትግራይ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ



www.ethiopianorthodox.org

# አባ ቆራይ

በሀገራችን ብዙ ታሪካዊ ሥራዎች የሚፈጸምባቸው ሥፍራዎች እንዳሉ የታመነ ነው እነዚህንም ዞሮ ተዟዙሮ ታሪካቸውን በመሰብሰብ ለማያውቃቸው ኢትዮጵያዊ በጋዜጣም ሆነ በመጽሔት ማሳወቅ የጋዜጠኞችና የደራስያን ኃላፊነትና ግዴታ ነው ።

ታሪካዊ ሥራዎች የተፈፀመባቸውና የሚፈጸምባቸው ሥፍራዎች አልፎ አልፎ አሁንም ስማቸው ተወስቶ የማይታወቅ ባለታሪክ ቦታዎች እንዳሉ የታመነ ነው ።

ከነዚህም አንዱ ከላይ በርእሱ የተጠቀሰው የአባ ቆራይ ገዳም ነው አባ ቆራይ የሚገኘው በትግራይ ክፍለ ሀገር በተምቤን አውራጃ በዐበራ ወረዳ በተለይ አዲ ራእሶት እየተባለ በሚጠራው ቀበሌ ነው ዓዲ ራእሶት ማለትም የራሶች አገር ማለት ሲሆን አባ ቆራይ ማለት ደግሞ በበሽታ ምክንያት የአካል ጉዳት የደረሰበት ማለት ነው ይህም የሰው ስም ነው ።

የዚህም ስም መነሻ በአጼ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት እኚህ አባ ቆራይ የተባሉ መነኩሴ ከላይ በተጠቀሰው ቀበሌ ተገልጸው ታዩ የእግርና የእጅ ጣት አልነበራቸውም ወንበር በምትመስል ድንጋይ ቁጭ ብለው ጸሎት ሲያደርሱ አንድ ሰው ያገኛቸዋል እርሱም ሄዶ ለሌሎች ሰዎች ይናገራል ብዙ ሰዎችም ይሰበሰባሉ ። ከተሰበሰቡት ሰዎች መካከል አንዱ አባቴ ከየት መጡ ስምዎስ ማን ይባላል? የሚል ጥያቄ አቀረበላቸው ።

እርሳቸውም ሲመልሱ ስሜ አባ ቆራይ እባላለሁ አገር ግን የለኝም የሚል ነበር እንግዲያስ ከዚህ ቦታ ይነሡና ወደሠፈራችን እንሂድ በዚያም ማረፊያ እንሰራልዎ ቢሉአቸው ማረፊያዬ ይህችና ናት ከዚህች ሥፍራ ፈጽሞ አልነሣም ብለው መለሱላቸው ።

ወዲያውኑ ምዕመናኑ እንደአንድ ቃል ተናጋሪ እንደ አንድ ልብ መካሪ ሆኖ ማር አጭደው እንጨት ቆርጠው በተቀመጡበት ዙሪያ ቤት ቀይሰው ሠሩላቸው አባ ቆራይ ግን ከተቀመጡበት ሳይነሡ ይጸልዩ ነበር እንጂ አንድም ቃል አልተናገሩም ።

ምዕመናኑ ቤቱን ሠርተው መዝጊያውን ገጥመው ወደየቤታቸው ተመልሰው ከሄዱ በኋላ ከመካከላቸው ምግብ እንዲያቀርብላቸው ዕጣ የደረሰው ሰውዩ ከአንድ ሰዓት በኋላ ምግብ ይዞላቸው ቢመጣ ኃጅው በብርሃን ተጥለቅልቆ ያገኘዋል ። ሊቀርብ ሲል እንደነበልባል እሳት ይገርፈዋል እርሱም ተመልሶ ወደቤቱ ይሄዳል ።

በበነጋታው ሰውየው ያየውንና የደረሰበትን ሁሉ ለምዕመናኑ ይነግራል ተሰብስበው ወደ አባ ቆራይ ሄደው ወደኃጅም ገብተው ቢመለከቱ አባ ቆራይ ከዚህ ዓለም በሞት ተሰናብተው ያገኙአቸዋል ። በአስከሬናቸውም ላይ የአባ ቆራይን አስከሬን ከዚህች ኃጅ ውስጥ እንድትቀብሩት ወደ ሌላ ቦታ ወይም ቤ ክርስቲያን ወስደን እንቀብራለን ብላችሁ እንዳታስቡ ነገሩን በድፍረት ብትፈጽሙት ግን በሀገሩ ላይ የእግዚአብሔር ቁጣ ታመጣላችሁ የሚል ጽሑፍ አገኙ ።

ምዕመናኑም በጽሑፉ መሠረት ከተኙባት ሥፍራ ላይ ቆፍረው ይቀብሩአቸውና ኃጅውን ዘግተው ይሄዳሉ ከዘመናት በኋላ ሁለት ባልናሚስት መቆም መራመድ የማይችል ሕፃን ይዘው ዐበል ለማጥመቅ በዚያች ቦታ ሲያልፉ የመሸባቸውና ኃጅው ባዶ ሰው ያሌለው መሆኑን አረጋግጠው ከፍተው ገብተው ያድራሉ እንደአጋጣሚ ሆኖ ሕፃኑ ከአባ ቆራይ መቃብር ላይ ተኝቶ ያድራል።

በበነጋታው ሁሉም ከተኙበት ተንቀሳቅሰው ይነግሉ ሕፃኑም ሲተኛ በሰው ሲነግ በሰው የነበረ አፈፍ ብሎ ይነግና ቀጥ ብሎ ይቆማል ። በዚህ ጊዜ አባት እናቱ ኀዘንና ደስታም ለጊዜው ያስደነግጣልና እንደቆሙ ጥቂት ደቂቃ ያህል ፈዘው የሚናገሩትም አጥተው ዝም አሉ ልጁ ግን ወዲያና ወዲህ እየዘለለና እየቦረቀ ይስቅ ይደስት ጀመር ።

አባት እናቱም ከጥቂት ደቂቃ ዝምታ በኋላ ከልጃቸው ጋር ወዲያና ወዲህ እየዘለሉ ደስታቸውን ይገልጹ ጀመር ይህንኑ አስደናቂ ተአምራትንም ወደመንደሩ ገብተው ለምዕመናኑ ተናገሩ ምዕመናኑም በእነርሱ አማካይነት አባ ቆራይን እጅግ በጣም አድርጎ ያከብራቸዋል ። ይልቁንም ዕለተ ዕረፍታቸውን ታኅሣሣ ፲፫ ቀን እጅግ በደመቀ ሁኔታ ያከብሩታል ።

ስለዚህ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ ክርስቲያን ካሏት ታሪካውያን ሥፍራዎች የአባ ቆራይ ቤ ክርስቲያን አንዱ ስለሆነ ምእመናን እንዲያውቁት በማለት በዛሬው እትማችን አቅርበነዋል ።

ሊቀ ትጉሐን ገ/ ክርስቶስ ኀ/ ማርያም



# የ፷ኛ ሰበካ ጉባኤ ሥምሪት በባሌ ሀ/ ስብከት

ሰባተኛው የሰበካ ጉባኤ ሥምሪት ከመጋቢት ፲፩ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ ም በ፲፯ አህጉረ ስብከት የተከናወነ መሆኑ ታውቋል ። በየአህጉረ ስብከቱ የተደረጉትን የሴሚናሮችን ውጤት አንድ በአንድ ዘርዝሮ ለማቅረብ ባይቻልም ከየአቅጣጫው የተነገረው ዜና እንደሚያስረዳው ካለፉት ዓመታት የበለጠ ውጤት በዚህ ዓመት እንደሚገኝ ተስፋ የሚጣልበት ነው ።

ለመገምገም ያህል በባሌ ሀ ስብከት የተከናወነውን ሴሚናር በአጭሩ ቀጥለን እንመለከታለን ።

ከመንበረ ፓትርያርክ የተላክነው ልዑካን በየአውራጃዎቹ እየተዘዋወርን የሁለት የሁለት ቀን ሴሚናር እንድናደርግ በታዘዝነው መሠረት መጋቢት ፲፫ ቀን ፲፱፻፸፱ ዓ ም ጧት ለአንድ ሰዓት ሩብ ጉዳይ ተነሥተን ከቀኑ ፲፩ ከ፴ ባሌ ዋና ከተማ ጎባ ደርሰን አድረናል ።

ከዚያ በኋላ በቅደም ተከተል በአምስት አውራጃዎች እየተዘዋወርን የሁለት የሁለት ቀን ሴሚናር አድርገናል ። በሴሚናሩ ላይ በዚያ ሀገረ ስብከት የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት በሰበካ ጉባኤ የተደራጁ መሆናቸውን ከየአውራጃዎች በቀረቡት ሪፖርቶች ለመረዳት ችለናል ።

በአንዳንድ አብያተ ክርስቲያናትም ያሉትን ችግሮች ለመመልከት በትተናል የደረሱትና የሚደርሱትም ችግሮች ከስብከተ ወንጌል እጥረት የተነሣ ነው ፡ በሀገረ ስብከቱ በስብከተ ወንጌል ሥራ ተቀጥረው በመደበኛነት የሚያስተምሩ አንድ መምህር ብቻ ናቸው የቀሩት ሰባክያን ግን የሚያስተምሩት የቢሮ ሥራ በሌለበት ቀን እሁድ ወይንም ቅዳሜ ከሰዓት በኋላ ነው ምክንያቱም የቢሮውንም ሥራ ደርበው የሚሠሩ በመሆናቸው ለስብከተ ወንጌል ሲሄዱ የቢሮው ሥራ ስለሚቀርባቸው ነው።

በዚሁ ሀገረ ስብከት በዋናው ከተማ በጐባና በአውራጃዎች ርእሰ ከተማ የሰንበት ት ቤቶች ተቋቁመዋል ነገር ግን በቂ አስተማሪ ስለማያገኙ ችግር ያለባቸው መሆናቸውን በተደረገው ሴሚናር ገልጸውልናል ፡ ወደ ካህናቱ ማስልጠኛ ሂደው ተምረው ሥልጥነው የተመለሱት ካህናት ለምን አያስተምሩም በማለት እኛ ለምናቀርበው ጥያቄ ከሰንበት ት ቤት ተማሮች የሚሰጠው መልስ ሠልጥነው የሚመለሱት ካህናት በዕውቀት ከእኛ ያልበለጡ በመሆናቸው እኛን ለማስተማር አይችሉም የሚል ነው ።

ከሰንበት ተማሮች መካከል አንዳንዱ ትምህርት ቤት በሚዘጋበት በክረምት ወቅት የመሠልጠን ዕድል

# የእግዚአብሔርን ቸርነት...

ከገጽ ፲፱ የቀጠለ

አገልግሎቱን በተሟላ ሁኔታ ለማካሄድ እንዲችል በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ በኩል ርዳታ ተጠይቆ ለሚቀጥለው ዓመት የጐደለውን ለማሟላት የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ቃል የገባ መሆኑን በባሌ ሀ/ስብከት በልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተጠሪ የሆኑት አቶ ፋንታ ኡራጉ ገልጸውልናል ።

የእግዚአብሔር ቸርነት በየጊዜው በየቦታው ይህንን በመሰለ መንገድ ይገለጻል ስለዚህ ክቡር ዳዊት የእግዚአብሔርን ቸርነት ተናገሩ ምሕረቱ ለዘለዓለም ነውና ብሎ እንደተናገረው ሁላችንም ስለ በእግዚአብሔር ቸርነትና አዳኝነት መናገር ይኖርብናል ።

የዜናው አቅራቢ
ቄስ ልማን ወርቅ በዛብህ



www.ethiopianorthodox.org

እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል ። ጉዳዩ አስፈላጊ በመሆኑ የሚመለከተው ክፍል ቢያብበት መልካም ነው እንላለን ።

በዚህ ሀገረ ስብከት የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ለልማት ሥራ አመች መሆናቸው የተረጋገጠ ነው። ይህንን በመመልከት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ የልማት ተወካይ መድቦ አንዳንድ የልማት ተግባሮችን በማቋቋም ላይ ይገኛል ።

በገናሌ አውራጃ በአዳባ ወረዳ የንብ ርዳታ ለመጀመር ጥናቱ የተጠናቀቀ ሲሆን በዋናው ከተማ በጐባ ደግሞ የሹራብ ሥራ ተቋቁሟል በመድኀኔ ዓለም ቤተ ክርስቲያን አጠገብ የሥርቶ ማሳያ እርሻ የተዘጋጀ ሲሆን በሌሎችም አድባራት ጥናት እየተጠና መሆኑን የልማትና ክርስቲያናዊ ተራድኦ መምሪያ ተወካይ አቶ ፋንታ ኡራጐ በሴሚናሩ ላይ ገልጸውታል ።

በዚህ ሀገረ ስብከት የአብነት መምህር አንድም አለመኖሩ በተደረገው ሴሚናር ላይ ስለተገለጸው ይህንን ችግር ለማቃለል ይቻል ዘንድ በገናሌ አውራጃ በዶዶላ ቅዱስ ገብረ ክርስቶስ አዳራሽ ውይይት ተደርጓል።

የባሌ ሀገረ ስብከት ከባዕድ ሀገር የሚጐራበት ቢሆንም በዚያ የሚገኙት ምዕመናን ለሀገራቸው ተአማኒያን መንፈሰ ጠንካሮች መሆናቸውን ተረድተናል ።

ከዚህ በተረፈ የባሌ ሀገረ ስብከት አየሩ ለጤና ተስማሚ ሕዝቡ ሰላማዊ የወገንና የሀገር ፍቅር ያለው ነው ፤ ክርስቲያኖችም በሰበካ ጉባኤ ቅጽ ተመዝግበው የሚፈለግባቸውን አስተዋጽኦ በወቅቱ ይከፍላሉ ። የሰንበት ተማሮችም በዕለተ ሰንበት በየሳምንቱ በታላላቅ በዓላት በቤተ ክርስቲያን እየተገኙ ይማራሉ ይዘምራሉ ።

የዜናው አቅራቢ
ቄ/ ልሣነ ወርቅ በዛብህ



# ኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ

የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ፤

ማሳሰቢያ ለምእመናን በሙሉ ፤

የኢትዮጵያን ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ታሪክ ፡ ጸዋትወ ዜማዎችንና ቅዳሴዎችን ፡ መንፈሳዊ ዛመናዊ መዝሙሮችን ፡ ትምህርቶችንና የልማት እንቅስቃሴዎችን ሁሉ እየተከታተለ በቋሚ እየቀረጸ ለቤተ ክርስቲያኒቱ ቋሚ ቅርስ ያስቀምጣል ። ይህንኑ ለሚፈልጉ ግለ ሰቦችም ሆኑ ድርጅቶች የካሴት ክር ላቀረቡ ያገልግሎት ሁለት ብር ብቻ ላላቀረቡ ግን ሰባት ብር በማስከፈል ይሰጣል ።
ለዚሁ ጥያቄ ቢኖርዎ ከድርጅቱ በመምጣት ወይም ስልክ በመደወል ለመረዳት ይቻላል ።

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ
የካሴት ሐዋርያ አገልግሎት ፤

የስልክ ቍ.
የመልእክት ሣ. ቍ. 3137
አዲስ አበባ ፤

www.ethiopianorthodox.org